# የጀግና ብያኔ በለቅሶ ዐውድ ላይ በሚከወን የፉከራ ቃል ግጥም ክዋኔና ይዘት ውስጥ በባህር ዳር ከተማ፣ በሰባታሚት ቀበሌ ማሳያነት

አስቴር ሙሉ[1]

**አጠቃሎ**

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በባህር ዳር ከተማ፣ በሰባታሚት ቀበሌ ለቅሶን አጋጣሚ አድርገው በሚከወኑ ቃል ግጥሞች ክዋኔና ይዘት ውስጥ የጀግናን ብያኔ መመርመር ነው። ጥናቱ በለቅሶው ዐውድ ውስጥ የፉከራ ቃል ግጥሞችን ክዋኔ ማሳየት፣ የጀግና መገለጫ እሴቶችን መለየት፣ በግጥሞች የተገለፀውን የጀግና ብያኔ ማሳየት የሚሉ ዝርዝር ዓላማዎች አሉት። ጥናቱ ዓይነታዊ ሲሆን መረጃዎች በምልከታና በቃለ መጠይቅ ተሰብስበውና የምርምር ጥያቄዎችን ከመመለስ አንፃር ተመድበው፣ በክዋኔያዊና ተግባራዊ ንድፈ ሃሳቦች ተተንትነዋል። የመረጃ ትንተና ውጤቱ እንደሚያሳየው የፉከራው ክዋኔ መግቢያ፣ ጊዜ ክወና (ሀተታ) እና መዝጊያ የሚል የታወቀ ቅርፅ አለው። በፉከራው ውስጥ የከዋኝን ሚና የሚጫወቱና ፉከራው የሚከወንበትን ፋይዳ የሚያጎሉ፣ በአንደኛና በሦስተኛ መደብ የቀረቡ ሁለት የትረካ አንፃሮች አሉ። ለቅሶን መሠረት አድርገው የሚከወኑ ፉከራዎች መሠረታዊ ትኩረታቸው ሟች በሕይወት እያለ የነበረውን ስብዕና መግለፅ ቢሆንም አልፎ አልፎ የሟችን ማንነት ከመግለፅ አንፃር ሥራዬ ተብሎ የሚደረግ ግነት አለባቸው። በሥነቃሉ የቀረበው የሟች አካላዊና መንፈሳዊ ማንነት ሙሉ በሙሉ የግለሰቡ መልክ አይደለም። ይልቁንስ ማኅበረሰቡ ባበጀው ባህል ውስጥ መገለጫ የሆኑ እሴቶች ትርጓሜ ነው። ጀግና የማኅበረሰቡን እሴትና ደንብ ማክበርና መጠበቅ የቻለ፣ማኅበረሰቡ የተጠየፋቸውን ባህርያት የተጠየፈና ለማስወገድ የሚሠራ ሰው መሆኑን የሚጠቁሙ ውጤቶች ተገኝተዋል። ከውጤቶች በመነሳት በከዋኝና በታዳሚ መካከል የሚደረግ የክዋኔ ተግባቦት የግለሰቡን ማንነት ብቻ ሳይሆን ማኅበረሰቡ የሚጠብቀውን ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያና ፖለቲካዊ ስብዕናና እሴት ለመትከል የሚደረግ ጥረት ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ተደርሷል። ርዕሰ ጉዳዩ ሰፊ በመሆኑ የባህል ጥናት ዕቅድ ያላቸው አካላት ጥናት ቢያካሂዱበት አዳዲስ ዕውቀቶችን ያበረክታሉ።

ቁልፍ ቃላት፡- [ጀግና፣ፉከራ፣ቃል፤ግጥም፣ክዋኔ]

## 1. መግቢያ

ይህ ጥናት የሰውን መሞት ሰበብ በማድረግ በተከወነ የለቅሶ ሥርዓት ውስጥ የተገኙ የስነቃል አይነቶች ላይ ትኩረት አድርጓል። ስነቃል የአንድ ማኅበረሰብ ልምድና አስተሳሰብ ከሚገለፅባቸው የሥነቃል ዘርፎች ውስጥ አንዱ ነው (ዘሪሁን 1992)። በተለያዩ አጋጣሚዎች ይከወናል። ከእነዚህ አጋጣሚዎች ውስጥ ለዚህ ጥናት መደረግ መነሻ የሆነው የለቅሶ ዐውድ አንዱ ነው። ሰዎች በተለያየ ምክንያት ሊያለቅሱ ይችላሉ። የሰውን መሞት መሠረት አድርጎ የሚከወን ለቅሶ ግን በብዙ ማኅበረሰቦች ዘንድ የራሱ ሥርዓትና ወግ ያለው፤ በክዋኔውም የከዋኙን ማኅበረሰብ እሳቤ የመግለፅ ከፍተኛ ሚና ያለው ነው። ለዚህም ምክንያቱ የለቅሶ ክዋኔ ሥርዓት፣ ከበራ ተብሎ በሚጠራው

---

[1] በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ሒውማቲስ ፋኩሊቲ፣በፎክሎር ትምህርት ክፍል መምህር፣ በፎክሎር የትምህርት መስክ ረዳት ፕሮፌሰር፤ ኢሜይል muluaster@yahoo.com

የፎክሎር ዘርፍ የሚመደብ በመሆኑ ነው። ከበራ ደግሞ sims and stephens (2005) እንደሚሉት የማኅበረሰብን እሳቤ ማሳየት አንድ ተግባሩ ነው።

### 1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህ ጥናት በዚህ ርዕስና ቦታ ለመደረጉ ምክንያቱ አጥኝዋ ለቦታው ያለኝ ቅርበትና ግላዊ ገጠመኝ ነው። ለጥናት የመረጥሁት ቦታ የምኖርበት አካባቢ በመሆኑና የማኅበራዊ ሕይወት አካል በመሆኔ የአንድን ግለሰብ መሞት ምክንያት በማድረግ ለቅሶ «ለመድረስ» ተገኝቼ ነበር። በወቅቱ በለቅሶው ላይ ይካሄድ የነበረው ክዋኔ አስቀድሞ ከማውቀው በእጅጉ የተለየ ሆኖ (የሚፈከርበት እንጅ የማይለቀስበት) ማግኘቴ በጥናት መስኩ ውስጥ በተደጋጋሚ ከታዩ የለቅሶ ክዋኔ አይነቶች ተጨማሪ ሌሎችም ያሉ መሆናቸውን ለመረዳትና ለማስረዳት አንድ መንገድ መሆኑን መገንዘቤ ጥናቱን ለማድረግ አነሳሽ ምክንያት ሆኖኛል።

### 1.2. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በባህር ዳር ከተማ፣ በሰባታሚት ቀበሌ ለቅሶን አጋጣሚ አድርገው በሚከወኑ የፉከራ ግጥሞች ክዋኔና ይዘት ውስጥ የሚገለጠውን የጀግና ብያኔ መመርመር ነው። ጥናቱ በዚህ ዋና ዓላማ ስር በለቅሶ ዐውድ ውስጥ የፉከራ ቃል ግጥሞች ክዋኔ ምን ሒደት አለው? በግጥሞች የተገለፀው የጀግና ብያኔ ምንድን ነው? በግጥሞች የሚገለፁት የጀግና መገለጫ እሴቶች ምንድን ናቸው? የሚሉ ዝርዝር ዓላማዎች አሉት።

### 1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ አንድ የክዋኔ አይነት የማስተዋወቅ ተግባር ያለው መሆኑ አንድ ጠቀሜታ ሲሆን ከዚህ ባሻገር ግን በመስኩ ቀጣይና ሰፊ ጥናት ለማድረግ ለሚሹ ተመራማሪዎች መነሻ ሊሆናቸው ይችላል። በተለይም የቃል ግጥሞች በባህሪያቸው በዘመንና በቦታ ምክንያት የመለዋወጥ ባህርይ ስላላቸው ወደፊት ባህልን ለሚያጠኑ ተመራማሪዎች የአሁኑን ዘመን የፉከራ ቃል ግጥሞች፣ ቅርፅ፣ ፋይዳ ወዘተ ከራሳቸው ዘመን ቃል ግጥሞች ጋር አነፃፅረው ለማጥናት ይጠቅማቸዋል። ተጠኚዎቹ ስለ አካባቢያቸውና ስለ ራሳቸው ያላቸውን አመለካከትና የሕይወት ፍልስፍና ለማወቅ ለሚፈልጉ ተመራማሪዎችና የተለያዩ አካላት የተወሰነ ፍንጭ ይሠጣል። በጊዜ ሂደት ባህሉ የመጥፋት ወይም በተወሰነ ደረጃ የመለወጥ እድል ቢያጋጥመው በዚህ ጥናት በመቀረሱ ምክንያት ለተከታዩ ትውልድ ለማስቀመጥ ይረዳል የሚለው የአጥኝዋ እምነት ነው።

### 1.4. የጥናቱ ወሰን

የተለያዩ ቃል መረጃ አቀባዮች እንደገለፁት በባህር ዳርና አካባቢዋ በሚገኙ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ፉከራ በተለያዩ ዐውዶች ላይ ይከወናል። ለምሳሌ ሠርግ፣ ክብረ በዓላት፣ ጠብ[2]፣ ፉከራ የሚከናወንባቸው ዐውዶች ናቸው። ይህ ጥናት ግን ባጋጠመ የጊዜ አቅም ውስንነትና ከአጥኝዋ ውስን ፍላጎት የተነሳ ትኩረቱን ያደረገው ለቅሶን መሰረት አድርገው በሚከወኑ የፉከራ ቃል ግጥሞች ላይ ብቻ ነው። መረጃውም በአንድ የለቅሶ ስርዓት ላይ ሲከወኑ ከነበሩ ቃል ግጥሞች ውስጥ የአንድን ግለሰብ ክዋኔ የተመለከተ ሲሆን ግለሰቡ ሊመረጥ የቻለው በወቅቱ ከተከወኑ ፉከራዎች

[2] ጠብ በተፈጠረበት ጊዜ በሚኖር የቁጣ ስሜት ፉከራ እንደስሜት መግለጫ ይከወናል።

ውስጥ የእሱ ረጅም የነበረ በመሆኑና ከታዳሚዎች ውስጥም አብዛኞቹ የሰውዬውን በዘርፉ ታዋቂነት ያረጋገጡ በመሆኑ ነው። በሌላ በኩል በባህር ዳር አካባቢ ማኅበረሰቡ «ሊፈከርላቸው ይገባል» የሚላቸውን ሰዎች ሞት መሰረት ተደርጎ፣ አስከሬን ከቤት ወጥቶ ወደ ቀብር እስኪደርስ፣ ለፍትሃት[3] በሚያርፍባቸው ቦታዎች ፉከራ ይካሄዳል። ይህ ጥናት ግን የተደረገው ከባህር ዳር ከተማ በስተደቡብ በሚገኝ ደብረብስራት ቅዱስ ገብርኤል (ጎርደማ ገብርኤል) ተብሎ በሚጠራ ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ነው። ለዚህም ዋና ምክንያቱ ቤተክርስቲያኑ ነባር በመሆኑ ለቀብርም ሆነ ለሌሎች ሃይማኖታዊ ግልጋሎት የሚጠቀሙበት ሰዎች በቤተክርስቲያኑ ዙሪያ በሚገኙ ሰባታሚት፣ ድሽት፣ ጎርደማ፣ አባራጅ በሚባሉ የገጠር ቀበሌዎች የሚኖሩ ነባር የአካባቢው ነዋሪዎች ናቸው። ይህም በአካባቢው ታዋቂና ተቀባይነት ያለውን ባህል ለማጥናት ዕድል የሚሰጥ ነው በሚል የአጥኚዋ እምነት የተነሳ በተመረጠው ቦታ ጥናት ለማድረግ አንዱ ምክንያት ነው።

### 1.5 የአጠናን ዘዴ

ጥናቱ ገላጭ የምርምር ዘዴን የተከተለ ሲሆን፣ የመረጃ መተንተኛ ዘዴው ደግሞ ዓይነታዊ ነው። ለዚህ ጥናት ተግባር ላይ የዋሉት የመረጃ ምንጮች ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ናቸው። ለቀዳማይ የመረጃ ምንጭነት ያገለገሉት የፉከራ ቃል ግጥሞች የተከወኑባቸው አውዶች፣ በክዋኔ ላይ የተሳተፉ ከዋኞችና ታዳሚዎች ናቸው። ቀዳማይ መረጃዎቹን ፉከራው በሚከናወንበት ቤተክርስቲያን በመገኘት በዐውዱ የተገኙትን ከዋኞችና ታዳሚዎች፣ በመመልከትና በመጠየቅ የቃል ግጥሞቹን የተመለከቱ መረጃዎች በተፈጥሯዊ መቼት በምልከታ እንዲሁም በቃለመጠይቅ ተሰብስበዋል። ለቃለ መጠይቅ የተመረጡት ሰዎች ዕድሜያቸው ከሰላሳ ስምንት (38) እስከ ሰባ (70) ዓመት የሆኑ ሰባት (7) ወንዶች እና ሁለት (2) ሴቶች በድምሩ ዘጠኝ (9) የቀበሌው ነዋሪዎች ስለፉከራና የአካባቢያቸው ልማድ በጥሩ ሁኔታ መግለጽ የሚችሉ፣ በልዩ ልዩ ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ባላቸው ተሳትፎ በሌሎች የማኅበረሰቡ አባላት ተቀባይነት ያላቸው ስለሆኑ ቁልፍ የመረጃ አቀባይ እንዲሆኑ በታለመ ናሙና አማካኝነት ተመርጠዋል። እነዚህ መረጃ ሰጪዎች ብቻ እንዲሆኑ የተደረገበት ምክንያትም መረጃው መደጋገም በመጀመሩ እንዳያሰለችና በተገለጹት መረጃ አቀባዮች የሚገኘው መረጃ ለትንተናው በቂ በመሆኑ ነው። በካልዓይ የመረጃ ምንጭነት መጻሕፍትና መጣጥፎች ጥቅም ላይ ውለዋል። መረጃ ምንጮቹ ከቤተ መጻሕፍት፣ ከኢንተርኔትና ከግለሰቦች የተሰበሰቡ ናቸው። ከተፈጥሯዊ መቼት መረጃ መሰብሰቡ የቃል ግጥሞቹን የአከዋወን ሂደት ለመረዳት አስችሏል።

ለዚህ ጥናት የመረጃ ትንተና ክዋኔ ተኮር /Performance theory/ ንድፈ ሐሳብ እና ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ (Functional theory) አገልግለዋል። ክዋኔያዊ ንድፈ ሐሳብ አንድ አጥኚ የሚያጠናው ቡድን የሚከውነውን ፎክሎር እንዴትና ለምን ሲል እንደሚከውነው ለማወቅ የሚያስችለው የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ነው። Sims እና Stephen (2005) ይህንን ሐሳብ “Analyzing performance enables folklorists to see how and why groups shape and share their traditional forms of expression” በማለት የፎክሎር ተመራማሪ ለክዋኔ ትኩረት ሰጥቶ የሚያጠናውን ፎክሎር ከመረመረ ተጠኚዎቹ እንዴትና ለምን ባህላዊ ጉዳዮቻቸውን እንደሚቀምሩና እንደሚግባቡ ማስተዋል እንደሚችል ገልጸዋል። ፈቃደ (1975፣ 66) ሥነቃልን

[3] ለሞተ ሰው የሚደረግ ሃይማኖታዊ ፀሎት

ከከዋኔ ውጪ ማጥናት ተገቢ አለመሆኑን አስመልክተው "... ኪነታዊ እሴቱን አንስተው ቃሉን ብቻ ቆዳውን ገፍፈው፣ ስጋውን በጭቀው፣ ደሙን አፍስሰው፣ አፅሙን ብቻ ያቀረቡ አይነት" ሲሉ እንደሚገልፁት ክዋኔ የፎክሎር ህልውና ከመሆኑ ባሻገር ክዋኔ በአንድ በተወሰነ ዐውድ ወይም ቡድን የሚቀርብን ጥበባዊ ገለጻ ለማጥናት ጠቀሜታው ከፍ ያለ በመሆኑ ክዋኔያዊ ንድፈ ሐሳብን በመጠቀም የፉከራ ቃል ግጥሙ ክዋኔ የማኅበረሰቡን አስተሳሰብ እንዴት በጥበብ እንደሚመራው ለማሳየት ተሞክሯል።

በተጨማሪም ጥናቱ ይዟቸው ከተነሳው የምርምር ጥያቄዎች አንጻር ተገቢውን ምላሽ ለማግኘት ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብም ጥቅም ላይ ውሏል። ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ማንኛውም ፎክሎር በሕይወት የሚቀጥለው ለማኅበረሰቡ አንዳች ፋይዳ ሲኖረው እንደሆነ የሚያስገነዝብ ንድፈሐሳብ ሲሆን በተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ መሰረት ፎክሎር እንደሚከወንበት ዐውድ የተለያዩ ተግባራት አሉት። ለምሳሌ Bascom (1954፣ 343-346) እንደሚሉት ፎክሎር አራት ዐበይት ተግባራት አሉት። እነዚህም የማዝናናት ወይም የማስደሰት (Amusement)፣ የባህልን ጠቀሜታ መግለፅ (Validating Culture)፣ የማስተማር (Education) እና የመግታት ወይም የመቆጣጠር (Maintaining Conformity to the accepted patterns of behavior) ናቸው ሲሉ ይገልፃሉ። በዚህ ጥናት ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ የፉከራ ቃል ግጥሞች፣ የጀግንነትን ምንነት ለመግለፅና የጀግንነት መገለጫ እሴቶችን ለመትከል ያበረከቱትን ጠቀሜታ ለማሳየት አገልግሎት ላይ ውሏል።

### 1.6. የምርምር *ሥነምግባር*

የመረጃ ስብሰባ ስራውን ከመጀመሬ በፊት ለቃለመጠይቁ አስፈላጊ የሆኑትን የመረጃ አቀባዮች በአካል በማግኘት እና ስልክ በመደወል የጥናቱን ዓላማ በማስረዳት ለቃለመጠይቅ አዘጋጅቻቸዋለሁ። በክዋኔው ዐውድ ተገኝቼ መረጃ ለመሰብሰብ ፈቃድና ትብብራቸውን ጠይቄያለሁ። በጽሑፉ ውስጥ ስማቸውን ለመጥቀስ ፈቃዳቸውን አግኝቻለሁ።

## 2. ክለሳ ድርሳናት

ይህ ክፍል ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር የተዛመዱ ፅሑፎች የቀረቡበት ነው። ሁለት ዋና ዋና ንዑሳን ርዕሶችን ይዟል። የመጀመሪያው ፅንሰ ሀሳባዊ ዳራ ሲሆን ሁለተኛው የቀደምት ጥናቶች ዳሰሳ ነው።

### 2.1. ፅንሰ ሀሳባዊ ማዕቀፍ

#### *2.1.1. የቃል ግጥም ምንነት*

ቃል ግጥም ሥነቃል ተብሎ በሚጠራው የፎክሎር ዘርፍ ውስጥ አንዱ አይነት ነው። ይህ የፎክሎር አይነት በአብዛኛው የዓለም ህዝብ ዘንድ ተከዋኝ ጥበብ ሲሆን ምንነቱን አስመልክቶ ባለሙያዎች የተለያዩ ብኔዎችን ሰጥተዋል። ለምሳሌ ብርሃኑ (1995፣ 31) «ቃልግጥም ሙዚቃዊነት በሚሰማባቸው በዘፈን፣ በቀረርቶ፣ በእንጉርጎሮ፣ … የሚከወኑ ጥበቦችን የሚጠቀልል … ነው። ቃልግጥም፣ እጅጉን የሚዘወተር፣ በጣሙን ደግሞ ልዩ ልዩ መልኮች ያሉት ጥበብ ነው" ብለውታል። Finneganም (1977፡16) «ቃላዊ ግጥም በቃል የሚተላለፍ ነው። በጽሑፍ ከዋለ ሥነግጥም ጋር ስናነፃፅረው ስርጭቱም ሆነ ክዋኔው በሕትመት ላይ የሰፈረ ሳይሆን በቃል የሚባል ነው » ሲሉ በይነዋል። ከላይ ከቀረቡ ብያኔዎች ቃል ግጥም በባህሪው ቃላዊ መሆኑን፣ ለትርጓሜውና ለአከዋወን ሥርዓቱ ዐውድን መሰረት የሚያደርግ የፎክሎር አይነት ነው የሚለውን ለመረዳት የሚቻል ሲሆን

Abrhams (1981፡ 66) በበኩላቸው «ቃል ግጥምን ለመበየን የሚያስችሉ ሦስት መሰረታዊ መንገዶች አደራረሱ፣ ስርጭቱ እና አከዋወኑ ናቸው። የዜማ ስልቱና አቀራረቡ እንደየባህሉ እና እንደየአካባቢው የተለያየ ሆኖ፤ በቃል ተደርሶ በቃል የሚከወን፣ በቃል የሚተላለፍና የሚሰራጭ፣ ግጥም ነው። የፍቅር ዘፈኖችን፣ የልጆች ዘፈኖችን፣ የሥራ ዘፈኖችን፣ ... ሀይማኖታዊ ዘፈኖችን እና ሌሎች ብዙ አይነቶችን የሚያጠቃልል ነው» ሲሉ ከሰጡት ብያኔ ደግሞ ቃል ግጥም ቃላዊ ብቻ ሳይሆን በቅርፅም ሆነ በይዘት ዐውዳዊ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡትን ብያኔዎች ስናስተውል ቃል ግጥም ቃላዊ፣ ዐውዳዊ፣ ኢመደበኛ ተስተላልፎ ያለው ባለብዙ ዘርፍ መሆኑን እንረዳለን። ይሁንና ከቃል ግጥም ብያኔ ጋር በተያያዘ ፈቃደ (1991፡ 84) የቃል ግጥምን በተመለከተ ብያኔ መስጠት አስቸጋሪ መሆኑን ገልጸው «ቃል ግጥም ማለት፣ አደራረሱ፣ አከዋወኑ፣ ተስተላልፎው እና አቀራረሱ ብዙ ጊዜ በቃልና በመዜም የሆነ፣ በዘፈን በሙሾ፣ በእንጉርጉሮና በሌሎች ተመሳሳይ ዜማዊ ቅርጾች ውስጥ የሚገኝ ሕዝባዊ ግጥም ነው»። የሚል ተግባራዊ ድንጋጌ /Operatonal definition ሰጥተዋል። ይህ ጥናትም የፈቃደን ብያኔ መሰረት አድርጎ ከሥነቃል ዘርፎች ውስጥ በመዜም በሚከወን ፉከራ በተባለ ዘርፍ ላይ ትኩረቱን አድርጓል።

### *2.1.2. ፉከራ ምንድን ነው?*

ፉከራ ከቃል ግጥም ዘርፎች ውስጥ አንዱ አይነት ነው፡ ይህ የቃል ግጥም ዘርፍ በቅርፁ ግጥማዊ የሆነ በቃል ተደርሶ፣ በቃል ሲተላለፍ የኖረ ባህላዊ የመከወኛ ዐውዱ በአመዛኙ ጦርነት፣ ነገር ግን ሰርግን፣ ለቅሶንና ሌሎች መሰል መሰባሰቦችንም በማኅበራዊ ዐውድነት የሚጠቀም የፎክሎር አይነት ነው። «ፉከራ»፣ ፎከረ ከሚል ግስ የተመሰረተ ውልድ ቃል ነው። የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር መዝገበ ቃላት (1993፣ 604) እንደሚለው ፎከረ፤ የፈፀመውን ጀብዱ በድንፋታ (ጀግንነትንና ወኔን በሚቀሰቅስ ሁኔታ) ተናገረ ማለት ሲሆን ፉከራ ደግሞ «አንድ ሰው ስለፈፀመው ጀብዱ እያነሳ በድንፋታ (ጀግንነትንና ወኔን በሚቀሰቅስ ሁኔታ) የሚናገረው ቃል የሚል ትርጉም አለው። ይህ የመዝገበ ቃላት ብያኔ ፉከራን በይዘትና በቅርፅ የገለፀ ነው። ትርጓሜው እንደሚለው ፉከራ በይዘቱ አንድን ከተለመደው ጉዳይ ከበድ ብሎ የተፈፀመ ተግባር (ጀብዱ) እንደሚይዝና በቅርፅ ደግሞ በሞቀ ስሜትና በጩኸት ድምፅ የሚነገር መሆኑን ይገልፃል። ማህተመ ሥላሴ (1957፣ 42) ፉከራን ሲበይኑ፡-

> ቀረርቶ ወይም ሽለላ ማለት የጦርነት ዘፈን ነው፤ወይም ወታደር በጌታው ፊት በሰልፍ መካከል እና በጨዋታ ላይ የወንዶችን ወኔ ለማነቃቃት በዜማ የሚያሰማው ቃል ነው። አቅራሪዎች በሰልፍ ውስጥ ወይም በግብር ላይ የጀግኖችን ልቡና በሽለላ እንደበገና አውታር እየቃኙ በየጦሩ ሜዳ የወደቁትን፣ ለሀገራቸው ታላላቅ ጀብዱዎች ሰርተው የሞቱትን የጦር ስልት በሆነ ዜማ፣ ባማረ ድምፅ ሚስጥር ያላቸውን ግጥሞች ባሰሙ ጊዜ፤ ባለሱሪዎቹን በልጓም እንደተያዙ ፈረሶች ያቅበጠብጣቸዋል፣ ደማቸው እንደፈላ አድርገው መቀመጥ እስኪሳናቸው፣ ቦታ እስኪጠባቸው ያሟሙቋቸዋል። በዚህ ጊዜ አላስችል ይላቸውና ባለወኔዎቹ ብድግ ብለው መፎከር ልማዳቸው ነው። ቀረርቶ እና ፉከራ አይለያይም፤ ቀረርቶ ይቀድማል ፉከራ ወይም ድንፋታ ይከተላል።

ብያኔው ፉከራ ለኢትዮጵያውያን ነባር የፎክሎር አይነት መሆኑን ይገልፃል። ይህ የፎክሎር አይነት ደግሞ ጀግንነትንና ወኔን ለማወደስ፣ እንዲሁም ለልጆች ለማውረስ ሲባል የሚከወን የጦርነትና

የወኔ ሙዚቃ መሆኑን፣ በጦርነት ብሎም በጨዋታ የሚከወን ዘውግ መሆኑን ጥቅሱ ያስረዳል። ከጥናቱ አካባቢ የተገኙ መረጃዎች ለፉከራ የሰጡት ብያኔ ከላይ ከቀረቡት ጋር በብዙ የሚመሳሰል ሲሆን «ፉከራ አንድ ሰው የራሱን ወይም የሌላን ሰው የተመሰገነ ሥራ እያነሳ፣ ሥራውን ለሰው ለማስመስገን፣ ጥሩ ሰሪው ክብር እንዲያገኝ፣ ደግሞ ሌላው እኔም እንዲህ ላርግ ብሎ ልቡ እንዲመኝ፣ ሞቅ ባለድምፅ፣ በአጀብ፣ ነፍጥ ታጥቆ ወዲያ እየኸደ ወዲህ እየተመለሰ የሚያረገው ጨዋታ፣ ሥራ ነው (ደባሱ ፈንታሁን፣ ቃለ መጠይቅ፣ 2013 ዓ.ም)።

በዚህ ብያኔ ፉከራ የበጎ መልካም ሥራ መዘከሪያና ማስተማሪያ መሆኑንና የራሱ የሆነ የአከዋወን ሥርዓት ያለው ጥበብ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ብያኔው ፉከራ የታወቀ የከወና መልክ ያለው መሆኑን ያሳያል። ይህም ክዋኔ የፎክሎር ዋና ባህርይ ነውና ፉከራ የታወቀ የከወና መልክ አለው ሲባል ፉከራ የፎክሎር ዘርፍ ነው የሚለውን የሚያስረዳ ነው።

### *2.1.3. ክዋኔ ምንድን ነው?*

ክዋኔ በፎክሎር ጥናት ውስጥ ዋና ፅንሰ ሐሳብ ነው። ምንነቱን አስመልክቶ የዘርፉ ባለሙያዎች የተለያዩ ሐሳቦችን ሰጥተዋል። ለምሳሌ Bauman (1975፡95) ክዋኔ የተግባቦት ወይም ያነጋገር ስልት መሆኑን ይጠቅሱና፣

> ከዋኙ ሥነቃሉን በሚያቀርብበት ባህል ልማዳዊ ሕግ መሠረት የሚጠበቅበትን ጥበብ እያሟላ፣ ታዳሚው ደግሞ ከሥነቃሉ የሚጠበቀውን ትውፊታዊ ውበት እያገኘ እርስ በእርስ የሚፈጥሩት ተግባቦት ነው። እንዲሁም ክዋኔ ታዳሚው የከዋኙን ባህላዊ ክህሎት ገምግሞ የሚመዘንበትና ልምድ የሚቀያየሩበት፣ ለከወናው መፍዘዝም ሆነ መድመቅ የታዳሚው ሚና ወሳኝ የሆነበት፣ ከቃላዊው ባሻገር የአካል እንቅስቃሴ፣ የፊት ገጽታ መለዋወጥ፣ የቅላፄ መቀያየርን የመሳሰሉ ቃል አልባ ተግባቦቶች የሚገልጹት ድርጊታዊ የተግባቦት ዘዴ ነው።

በማለት ያብራሩታል።

Kapchan (1995፣ 479) በበኩላቸው፡-

> ክዋኔ ውበታዊ የሆነ የድርጊት ባህርይ፣ የንግግር ዘዴ፣በአካል የሚከወን፣ በጊዜና በቦታ የተገደበ፣ በታወቀ መዋቅር በከዋኞች የሚቀርብ ከመሆኑም በተጨማሪ በተደጋጋሚ የሚፈጸም፣ በግልና በቡድን የሚዋቀር የማንነት ማሳያ ነው። በሌላ በኩል ክዋኔ የፎክሎርን ፅንሰሐሳብ የሚመራ ውበት ያለው ጥበባዊ ድርጊት ነው። ይኸውም የፎክሎር ጥበባዊ ድርጊት ከዋኝ፣ ቦታ፣ ተመልካችና የከዋኔውን ሁኔታ የሚይዝ ነው ይላሉ።

ከላይ ከቀረቡ ብያኔዎች ክዋኔ ለፎክሎር መሰረታዊ ነገር መሆኑንና ፅንሰ ሀሳቡን ለመረዳት ከዋኝ፣ ታዳሚና ዐውድ የሚባሉ ሦስት ነጥቦችን ማስተዋል እንደሚገባ መረዳት ይቻላል። ይህ ጥናትም የለቅሶን ክዋኔ መመርመር አንድ አላማው እንደመሆኑ ከላይ የቀረቡ የክዋኔ ብያኔዎችንና በክዋኔ ውስጥ ሊተኮርባቸው የሚገቡ ነጥቦችን መሰረት በማድረግ መረጃዎች ተተንትነዋል።

### *2.1.4. ጀግና ምንድን ነው?*

ጀግንነትን በተመለከተ እስካሁን ሁሉንም ሊያግባባ የሚችል ትርጓሜ የለም። ለዚህም ምክንያቱ ጀግንነት ማኅበረ ባህላዊ ዐውድን መሰረት አድርጎ የሚበየን ፅንሰ ሀሳብ በመሆኑ ነው። በዚህም የተነሳ ለአንድ ባህል ጀግና የሆነ ግለሰብ ለሌላው አጥፊ ሊሆን ይችላል። ከዚህ ጋር በተያያዘ Luigi (2006) የአንዱ ጀግና ለሌላው ምንም ሊሆን ስለሚችል የጀግንነትን ትርጓሜ ከዐውድ ውጭ መመልከት እንደማይቻል ይገልፃሉ። Thomson (2005) ደግሞ የባህል ጀግኖችን በሰው ልጅ ነገሮችን የመቋቋምና የማለፍ ደረጃ መቼት የሚወክሉ ናቸው ብሎ መበየን እንደሚቻል ያስረዳሉ።

ይሁንና ምንም እንኳን ለፅንሰ ሀሳቡ ሁሉንም ሰው ጠቅልሎ የሚይዝ አንድ ፍቺ መስጠት ባይቻል ለመግባባት የሚያበቁ ብያኔዎች ተሰጥተዋል። ለምሳሌ Carlyle (1998) በዐለም ታሪክ ውስጥ ስሙ የሚታወቅ ሰው ጀግና ይባላል ሲሉ Campbell (1990) ደግሞ በሁሉም ሚቶች ውስጥ የሚገኙ ጀግኖች ስለ አንድ ጀግና የሚገልፁ ናቸው። ይህ ጀግናም ተዓምራትን የማድረግ ተምሳሌት የሆነ (magical figure) ከሚስጥራዊ ተጋድሎዎች በረከትን የሚያገኝና ካገኘው በረከት ሕዝቡን የሚባርክ ሰው እንደሆነ ያስረዳሉ። Roebuck (2008)ም ጀግና ማለት ልዕለ ባህርይ ያላቸው ተራ ሰዎች ስያሜ ነው ሲሉ በይነዋል። የኢትዮጵያ ቋንቋ ጥናትና ምርምር መዝገበ ቃላት (1993፣ 488) በበኩሉ ጀግና የሚለውን ቃል "ለሃገር፣ ለወገን መስዋዕትነት ከፍሎ ጥሩ ተግባር ያከናወነ ወኔ፣ ድፍረት በሚጠይቅ ሁኔታ ላይ ጀብዱ የሠራ፤ ብርታትን በሚጠይቅ ሥራ ላይ ችግርን ተቋቁሞ ለውጤት የበቃ" ሲለው Labarge (2010) የተባሉ ፀሐፊ ጀግና የሚለው ቃል የመጣው ከግሪክ እንደሆነ ገልፀው ጀግና ማለት ሊሞት የሚችል ነገር ግን ከመሞቱ በፊት ከሰው ልጆች የተለመደ ነገር ወጣ ባለመልኩ የማይሞት ሥራ የሚሠራ ሰው ነው ሲሉ በይነዋል።

Miriam (2017)ም "ጀግኖች ማኅበረሰቡ በጣም የሚያደንቃቸውን እሴቶች እና እምነቶችን የሚወክሉ ሰዎች መሆናቸውን "heroes represent the values and beliefs that society admires most" በማለት አስፍረዋል። ይህ እሳቤ ጀግኖች የበቀሉበትን ማኅበረሰብ እሴቶችና እምነቶች የሚያከብሩና ለእነሱም ወኪል ሆነው እስከመቆም ድረስ በማኅበረሰባቸው እምነት የተጣለባቸው ሰዎች እንደሆኑ ያሳያል። ከዚህ በመነሳት አንድ ሰው ጀግና ለመባል የሚገለፅባቸው ባህርያት እንዳሉት ለመረዳት የሚቻል ሲሆን እነኚህ መገለጫዎች እንደየማኅበረሰቡ ሁኔታ የተለያዩ መሆናቸው Orrin (1948) ያስረዳሉ።

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ብያኔዎች በመነሳት ጀግና የማኅበረሰቡን እሴቶችና እምነቶች ወክሎ በመቆሙ የተለየ ክብርና ዋጋ ያለው ግለሰብ ነው የሚለውን መረዳት ይቻላል። በዚህ ጥናትም ጀግና ማኅበረሰቡ በጣም የሚያደንቃቸውን እሴቶች እና እምነቶችን የሚወክሉ ሰዎች መጠሪያ ሲሆን አንድ ሰው ጀግና ለመባል የሚገለፅባቸው ባህርያትም እንዳሉት Miriam (2017) እና Orrin (1948) የሰጧቸው ብያኔዎች ያስረዳሉ።

### 2.2. የቀደምት ተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

የዚህ ጥናት ትኩረት ጀግና የሚል እንደመሆኑና ጀግንነትን ለማሳየት የተመረጠው የፎክሎር ዘርፍም ፉከራ እንደመሆኑ ለጥናቱ ቅርበት ይኖራቸዋል ያልኋቸውን ጥናቶች ለማግኘት ሞክሬያለሁ። በመጀመሪያ ዳሰሳ ያደረግሁት ባይለየኝ (2001) «ኦቴኖ፡- የአኙዋ ባህላዊ ጀግና» የተሰኘውን ጥናት ነው። የዚህ ጥናት ትኩረት በአኙዋ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚተረክና «ኦቴኖ» ተብሎ የሚጠራን

ጀግና ታሪክ ሥነጽሑፋዊ ትርጓሜ መመርመር ነው። ጥናቱ ኦቴኖ ምን አይነት ጀግና ነው? በባለ ታሪኩ ገድል፣ እጣና እድል እንዲሁም በተሰጡት ሰብአዊ ባህርያት አማካኝነት አኙዋዎች ስለ ተፈጥሯዊው ዓለም ሥርአትና ስለ እራሳቸው ያላቸውን ግንዛቤና እምነት እንዴት ይገልፁታል? የሚሉ ጥያቄዎችን አንስቶ መልስ ሰጥቷል። ባይለየኝ በዚህ ጥናታቸው ባህላዊ ጀግና ምንድን ነው? አኙዋዎችና እምነታቸው ምን ይመስላል? የኦቴኖ ታሪክ ምንድን ነው? የተሰኙ ጥያቄዎችን አንስተው በትንታኔ ካሳዩ በኋላ በውጤቱ ኦቴኖ መንፈሳዊና ሰብአዊ ፍጡር መሆኑን አሳይተዋል። ይህ ጥናት በዋናነት የአንድን ማኅበረሰብ የጀግንነት እሳቤ ያሳየ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ይመሳሰላል። ይሁንና ጥናቱ ለጀግንነት መመርመሪያ የተጠቀመው የፎክሎር አይነት ትረካ በመሆኑ፣ ዋና ትኩረቱም የአንድን ገፀባህርይ ምስል ማሳየት መሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር የተለየ ያደርገዋል።

ከላይ ከቀረበው ጥናት በተጨማሪ ከዚህ ጥናት ጋር ተዛምዶ አለው ስል የከለስኩት ሞገስ ሚካኤል (2002) «የላይ አርማጭሆ ማኅበረሰብ የጀግና የቀብር ሥነስርዓት» የሚል ጥናት ነው። የጥናቱ ዋና ዓላማ "በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረገውን የጀግና የቀብር ሥነስርዓት፣ በሥርዓቱ ላይ የሚደረገውን የቀረርቶ እና የፉከራ ክዋኔ በቪዲዮ በመቅረፅ፣ በቴፕ በመቅዳት፣ ፎቶግራፍ በማንሳት እና ጥናቱንም በፅሑፍ በማዘጋጀት እንዲቀረስ ማድረግ" የሚል ነው። አጥኝው ለጀግና የሚደረገውን የለቅሶ ሥርዓት ያሳያሉ ሲሉ የሰበሰቧቸውን መረጃዎች ቅድመ፣ ጊዜና ድህረ ሞት ዝግጅት በሚሉ ሦስት ክፍሎች መድበው ተንትነዋል። በጥናቱ «የቅድመ ሞት ዝግጅት» በሚል ርዕስ ስር «የኑዛዜ ስርዓት አፈፃፀም» እና «ለዋናው ለቅሶ እና ለለቀስተኛ ማስተናገጃ የሚደረጉ ዝግጅቶች» የሚሉትን፤ በ«ጊዜ ሞት» ስር «በምሽት የሚካሔዱ ስነስርዓቶች»፣«በንጋት የሚካሔዱ ስነ ስርዓቶች»፣ «በአስከሬን ጉዞ ወቅት የሚከናወኑ ስነስርዓቶች» እና «ከቀብር በኋላ የሚከናወኑ ስነስርዓቶች» ሲሉ ትንታኔ አቅርበዋል። ይህ ጥናት ትኩረቱ፣ «ጀግና» የሚለው ፅንሰ ሀሳብ መሆኑና በዐውድነትም ለቅሶን መጠቀሙ ከእኔ ጥናት ጋር ቢያመሳስለውም ጥናቱ የአርማጭሆን ማኅበረሰብ የጀግና የለቅሶ ሥርአት ምን እንደሚመስል ከማሳየት ባሻገር በጀግና ብያኔና የጀግና መገለጫ እሴቶችን አለማየቱ ከቦታና ከትኩረት አቅጣጫ አንፃር ልዩነት ያለው ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

በሦስተኛነት ከዚህ ጥናት ጋር በብዙ ተመሳስሎ ያለው ሆኖ ያገኘሁት ጥናት በጌትነት ይርሳው (2011) «የጀግና እሳቤ በይጎማ ሁለቱ ማሕበረሰብ የጀግና የለቅሶ ዐውድ ውስጥ በሚከወኑ የፉከራ ቃል-ግጥሞች ይዘትና ክዋኔ ውስጥ» በሚል ርእስ የተሠራ ጥናት ነው። በትንታኔውም ጀግና ማለት ማኅበረሰቡ የእለት ተዕለት ሕይወቱን ለመምራት በየተሰማራባቸው ልዩ ልዩ የሥራ መስኮችና በሚከውናቸው ሌሎች ዘወትራዊ ተግባራት ማኅበረሰቡን የሚመሩና ማኅበረሰቡ የሚመካባቸው ግለሰቦች ናቸው። ባለፉት ጊዚያቶች በተለያየ መልኩ በማኅበረሰቡ ላይ የተደቀኑ ችግሮች (ፈተናዎች) ለእነኚህ ጀግኖች መፈጠር ዋነኛ ምክንያት ናቸው። ቃል-ግጥሞች፣ የቤተሰብና የሃይማኖት ተቋማት ደግሞ ልጆች ጀግና ሆነው እንዲቀረፁ የማይተካ ድርሻ አላቸው። ማኅበረሰቡ ይሄን የጀግንነት ልማዱን የሚያስጠብቀው ጀግናዎቹን ከፍ አድርጎ በመመልከትና ተገቢውን እውቅና በመስጠት ነው። የጀግኖች መኖርም በዋናነት ማኅበረሰቡ ለከፋ ድህነት እንዳይጋለጥ፣ በማኅበረሰቡ ዘንድ ሰላም እንዲሰፍን፤ ማኅበራዊ ትስስሩ እንዲጠናከር፣ ማኅበረሰቡ በቀላሉ እርስ በእርሱ እንዳይጎዳዳና መፈናቀል እንዳይገጥመው፣ ሥርዓት ባለው ሁኔታና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እንዲተዳደር በማድረግ ረገድ ጉልህ ድርሻ አላቸው የሚሉ ውጤቶች ተገኝተዋል።

የጌትነት ጥናት ባነሳው ርዕሰ ጉዳይ፣ በተሰራበት አካባቢ፣ እና ያነሳውን ርዕሰ ጉዳይ ለማየት በመረጠው የፎክሎር ዘርፍ አንፃር ከእኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላል። ይሁንና ጥናቱ ምንም እንኳን የጀግና አሳቤ ምን ይመስላል የሚለውን የመረመረ መሆኑ ቢያመሳስለንም የእሱ ጥናት ሀሳቡን ለመመርመር የቀረፀው አላማና ጥናቱን የፈተሸበት ወሰን ከእኔ ጥናት ይልቅ ሰፊ ነው። ይህም በሁለቱ ጥናቶች መካከል የተገኙ ውጤቶችን አይነት የተለያየ እንዲሆን አድርጎታል።

## 3. ትንተና

### 3.1. የፉከራ ግጥሙ ክዋኔ ምን ይመስላል?

ክዋኔ በፎክሎር ጥናት ውስጥ ዋና ፅንሰ ሐሳብ ነው። በKapchan (1995፣ 479) ብያኔ ክዋኔ፣ የፎክሎርን ፅንሰሐሳብ የሚመራ ውበት ያለው ጥበባዊ ድርጊት ነው። በውስጡ ዐውድ፣ ከዋኝ፣ ታዳሚ የሚባሉ ሦስት መሰረታዊ ነጥቦች ያሉትና ራሱም የታወቀ ቅርፅ ያለው መሆኑ ተጠቁሟል። በዚህ ጥናት እነዚህን መሠረታዊ ነጥቦች እና የክዋኔው ቅርፅ መሠረት በማድረግ መረጃው እንደሚከተለው ተተንትኗል።

***ዐውድ፡-*** *ዐውድ ፎክሎሩ የሚደረግበትን ቦታና ጊዜ አጠቃላይ ሁኔታ ይመለከታል። በመሆኑም በዚህ ጥናት ትኩረት የተደረገበት ርዕሰ ጉዳይ (ፉከራ) የተደረገው የአንድን ግለሰብ መሞት መሰረት አድርጎ ጎርደማ ገብርኤል በተባለ ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ነው። ጎርደማ ገብርኤል ቤተክርስቲያን በባህር ዳር ከተማ በስተደቡብ ይገኛል። የቃል መረጃ አቀባዮች እንደሚገልጡት ቤተክርስቲያኑ ከ1970 ዓ.ም በፊት የተቋቋመ ሲሆን በዙሪያው በግብርና ሥራ የሚተዳደሩ ማኅበረሰቦች የሚኖሩባቸው ጎርደማ፣ ድሸት፣ አባራጅ፣ ሳሬዋርካ፣ ሰባታሚት ወዘተ የተባሉ ከተማ ቀመስ የገጠር ቀበሌዎች ይገኛሉ። በእነዚህ ቀበሌዎች ከሚኖሩ ሰዎች ብዙዎቹ የክርስትና እምነት ተከታዮች ሲሆኑ ሕፃናትን ክርስትና ማስነሳት፣ የነፍስ አባት ማበጀት፣ ሲሞቱ መቀበርና የመሳሰሉ ማናቸውንም ሃይማኖታዊ ግልጋሎቶች የሚያገኙት ጎርደማ ገብርኤል ተብሎ ከሚጠራው ቤተክርስቲያን ነው።*

በዚህም መሰረት በመስኩ የሥነቃል ባህርያት ብለው ከሚያነሷቸው ነጥቦች ውስጥ ሰበብ ፈላጊነት አንዱ ነው (ዘሪሁን፣ 1992)። ይህ ጥናት የተደረገው ከሰባታሚት ቀበሌ የሞቱ **አስናቀው ሆነ** የተባሉ ግለሰብን ሞት ሰበብ (ምክንያት) አድርጎ በተከወነ የለቅሶ ሥርዓት ላይ የተከወኑ የፉከራ ቃል ግጥሞች ላይ ነው። ለቅሶው የዕለት ሞት አልነበረም። ይልቁንም ሟቹ ከዚህ ዓለም የተለዩ ጥር 13፣ 2011 ዓ.ም ላይ ነበር። ይሁንና በአንድ በኩል ጊዜው የጥምቀት በዓል ሰሞን በመሆኑ በሌላ በኩልም ባህሉ ይህንን የሚፈልግ በመሆኑ በተለያዩ ምክንያቶች (በርቀት፣ ባለመስማት፣ በግል ሥራ ምክንያት) በቀብሩ ቀን ያልተገኙ ሰዎች "እርማቸውን እንዲያወጡ"[4] ተብሎ የተዘጋጀ «ምስል» (የቀጠሮ ለቅሶ)[5] ነበር። የቀጠሮ ለቅሶው የተካሄደው ቅዳሜ የካቲት ሦስት፣ 2011 ዓ.ም ሲሆን ክዋኔው የተጀመረው ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት አካባቢ ረፋድፋድ ሲል ነው። ከሟቹ ቤተሰቦች እና

---

[4] የሰውን መሞት አውቀው አልቅሰው ልባቸው እንዲቆርጥላቸው ማድረጊያ ስርዓት

[5] ምስል፣የአካባቢው ማኅበረሰብ የቀጠሮ ለቅሶውን የሚጠራበት ስያሜ ነው፤ ሞት ድንገተኛ ክስተት እንደመሆኑ አንድ ሰው በሞተ ጊዜ በለቅሶው መገኘት የሚገባው ጎረቤት፣ዘመድ ወዳጅ በተለያየ ምክንያት ቀብር ላይ ላይገኝ ይችላል። ይህንን ሁኔታም ግምት ውስጥ በማስገባት ከቀብር በኋላ ባሉ ቀናት በተቻለ መጠን ለብዙ ሰው ማዕከላዊ የሆነ ቦታ (ቤተክርስቲያን) ተመርጦ የሚካሄድ የለቅሶ ስርዓት ነው፡፡

ከለቅሶው ከታደሙ ሰዎች እንደተገኘው መረጃ አስቀድሞ በተለያየ ቦታ ለሚኖሩ የሟች ዘመዶችና ወዳጆች የ«ምስል» ቀን መች እንደሆነ ተነግሯል (በለጠ አስናቀው፣15/06/2011)።

በመሆኑም በለቅሶው ታዳሚ የሆኑ ሰዎች ከተለያየ አቅጣጫ የሚመጡ በመሆኑ እንደመኖሪያው ቅርበትና ርቀት ፊትና ኋላ እየሆኑ በመድረሳቸው፣ በቦታው ሰው መሰባሰብ የጀመረው ቀስ በቀስ ነው። በዚህ ሁኔታ ከጅምሩ ጥቂት የነበረው የሰው ቁጥር እየጨመረ መጥቶ የታዳሚው ቁጥር በረከተ። የሰውን ቁጥር መብዛት መሠረት አድርጎ በከዋኝና ታዳሚ ድምፅ፣ እንቅስቃሴ፣ የሚደረገው የለቅሶው ክዋኔ እየደመቀ መጣ (ምልከታ፣ 03/06/2011) ። ክዋኔው ክብ በሠራ የሰው አጥር ውስጥ የሚከወን ሲሆን የሟቹ ልጆች (ሁለት ሴትና ሦስት ወንድ) ሴቶች የሟች አባታቸውን ልብስ (ኮትና ሸሚዝ) ከጀርባቸው ደርበውና ፎቶው ለታዳሚ እንዲታይ ምስሉን ወደ ፊት አዞረው፣ ወንዶች ደግሞ ካቦርት ለብሰው በክቡ ውስጥ እየዞሩ ያለቅሳሉ። የሟቹ የቅርብ ዘመዶች ልጆችን ተከትለው በክቡ ውስጥ እያለቀሱ ይዞራሉ። ለለቅሶ የመጡ ጥቂት ሰዎች በየተራ እየተቀባበሉ ሙሾ[6] እያወረዱ፣ ብዙው ሰው ደግሞ ሙሾን እየተቀበለ ሲለቀስ ቆየ። ሰው ሲበዛና ለቅሶው እየደመቀ ሲመጣ ፉከራ ተጀመረ።

**ከዋኝ፡**-ከዋኝ የአንድ ባህል ባለቤት የሆነና ባህሉ በሚፈቅደው መሠረት ፎክሎሩን የሚከውን ሰው ነው። ከዋኞች የሚያነሷቸው ርዕሰ ጉዳዮችና የሚከውኗቸው ክዋኔዎች ማንነታቸውን በመግለጽ ረገድ የራሳቸው የሆነ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ Bronner (1988)። መረጃዎች እንደሚገልፁት ፉከራ ሁሉም ሰው ሊከውነው የሚችል የሥነቃል ዘርፍ አይደለም። ይልቁንም የተመረጡ ከዋኞች አሉት (ቃለመጠይቅ፣ በላይነህ ፈንታሁን፣15/06/2011፣ በባህርዳር)። የተገኘው የቃል መረጃ እንደሚገልፀው በወቅቱ ሥነቃሉን ሲከውኑ የነበሩ ከዋኞች ሁለት አይነት ናቸው። አንዳንዶቹ ዋና መተዳደሪያቸው ግብርና የሆነ ነገር ግን ፉከራን አጋጣሚዎች በፈቀዱበት ጊዜ የሚከውኑ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ መፎከር ዋና የገቢ ምንጫቸው የሆነ የመፎከርን ዕውቀት ሥራዬ ብለው እያዳበሩ የሚኖሩ የአካባቢው ተወላጅ የሆኑ ባይሆኑም እንኳን ፉከራውን በሚያቀርቡበት ማኅበረሰብ ውስጥ የሚፎከርለትን ሰው የሕይወት ታሪክ ጠይቀው ግጥሙን የሚያዘጋጁ ናቸው። በዚህ ጥናት ትኩረት የተደረገበት ግጥም ከዋኝ የአካባቢው ተወላጅ ሲሆን መፎከርን የገቢ ምንጩ አድርጎ የሚገለገል ሰው ነው። ለፉከራው ሲመጣ ይህ ነው የሚባል የተለየ አለባበስ ባይለብስም በዋናነት ግን ከላሽ የተባለውን መሣሪያ ይዟል። ክዋኔውን በሚያካሄድበት ጊዜ የመሣሪያውን አፈሙዝ ወደ ላይ ቀና አድርጎ፣ መሣሪያውን ከትከሻው አጣብቆ ይዞ፣ በከፍተኛ፣ የቁጣ፣ የደም ፍላትና የድንፋታ ስሜት ወደ ፊትና ወደ ኋላ እየተንቀሳቀሰ፣ አንዴ ቁጭ ሌላ ጊዜ ቆም እያለ፣ በድርጊትና በእንቅስቃሴው ታዳሚዎችን ይመራል።

***ታዳሚ፡***- ታዳሚዎች ፎክሎሩ በሚከወንበት አካባቢ ተገኝተው ለከዋኙ ድርጊት አንዳች ምላሽ የሚሰጡ ሰዎች ናቸው። ተሳታፊዎች በራሳቸው መንገድ ክዋኔውን ሲረዱት አሉታዊ ወይም አወንታዊ መልስ ይሰጣሉ (Finnegan, 1992) ። አንድ ክዋኔ በሚከወን ጊዜ ክዋኔው ለሚካሄድበት መቼት ተሳታፊዎች ባህሪያትና ምላሽ ትኩረት መስጠት ያሻል። በቃለመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች እንደገለፁት በወቅቱ በክዋኔው ውስጥ የነበሩ ታዳሚዎች የሟቹ ልጆች፣ እህት ወንድሞች፣

[6] ለሞተ ሰው የሚደረግ በግጥምና ዜማ የተሰናዳ ለቅሶ በፎክሎር ዘርፍ ከሚጠኑ አይነቶች አንዱ ነው፡፡

«አገቡሾች» (በጋብቻ የተዛመዱ ሰዎች)፣ ጎረቤቶች ከሟቹና የሟቹ ቤተሰቦች በተለያየ ምክንያት ትውውቅ ያላቸው ሰዎች ነበሩ (ፀጋ አስናቀው፣ ይመኑ እውነቴ፣13/06/2011፣ ቃለ መጠይቅ፣ ባህር ዳር)።

ከታዳሚዎቹ ውስጥ በዖታ ረገድ ወንዶች ከዋኙ የሚያወርዳቸውን ግጥሞች በመቀበል «ልክ ነው»! «ይል ነበር»! የሚሉ በድምፅ መጠንና በአካል እንቅስቃሴ ቁጣን፣ ኩራትን በሚያሳይ መልክ ምላሾችን ሲሰጡና ፎካሪው የሚናገረው ነገር ትክክለኛ መሆኑን ሲያረጋግጡ ሴቶች ደግሞ፣ «እልልል . . . » በማለት ክዋኔው እንዲቀጥል የየራሳቸውን ሚና አላቸው።

### *3.1.1. የፉከራ ክዋኔው ቅርፅ*

የክዋኔያዊ ንድፈ ሐሳብ አራማጆች ማንኛውም ክዋኔ የራሱ የሆነ የመክፈቻና የመዝጊያ ቅርፅ አለው ሲሉ Hayms (1975) ይገልፃሉ። ጥናቱ ባተኮረበት ክዋኔ የታየው እያንዳንዱ የፉከራ ሥርዓትም መግቢያ፣ መሃልና መደምደሚያ ያለው መሆኑን ለማየት ተችሏል። ከዋኙ ፉከራ መጀመሩን በሚገልፅ አኳኃን ቀጥሎ የቀረቡ ስንኞችን ደርድሯል።

እስኪ ብረት አውርድ ጀግና
አካኪ ዘራፍ
አካኪ ዘራፍ
በሃገር ጥቅሻ በአራቱ ማዕዘን እስኪ እንጀምረው በድንበር ይዘን
በመጀመሪያ ወደ ምስራቅ ከተፈጠረ ችጋር ማያውቅ
በዚህም ቢሆን በሰሜንዋ ነገር ከስርዋ ከመነሻዋ
በዚህ በደቡብ አታሳንሰው አምጣው ስሙን፣ ያንን ገበሬ ያንን ዘላን[7]
ደግሞም በምዕራብ ላንሳው ስሙን፣ የታፈን ወንድም አቶ አስኔዋን
ልበለው?

በዚህ ግጥም ልክ ከዋኙ የመጀመሪያውም መስመር "እስኪ ብረት አውርድ ጀግና" የሚለውን ስንኝ ሲናገር ከአጠገቡ ያሉ «መሣሪያ» (የጦር መሣሪያ) የያዙ ሰዎች ከትከሻቸው ላይ አስቀምጠውት የነበረውን መሣሪያ ወደ ታች አውርደው በእጃቸው ይይዙታል። ከዚያም ቀጣይ ስንኞች እንደሚገልፁት ከዋኙ በግጥሙ የመግቢያ ክፍል በክዋኔው የሟቹን ሁለንተናዊ ማንነት ለመግለፅ መዘጋጀቱን በመግለፅ ታዳሚውን ያዘጋጃል። ማዘጋጀት ብቻ አይደለም። *«ልበለው? »* ሲል የታዳሚውን ስምምነት ይጠይቃል። ይህን ጊዜ ታዳሚው *«በለው! »*፣ *«ልክ ነው! »* ሲል ስምምነቱን ይገልፃል። ስምምነቱ ግለሰቡ በእነዚህ ጉዳዮች ሊወደስ የሚገባው መሆኑን ታዳሚው ማመኑን የሚያሳይ ነው። እነዚህ ማኅበረሰብ ያመነባቸው ነጥቦች ደግሞ ሃብትን፣ *«ከተፈጠረ ችጋር ማያውቅ»*፣ ከማንነት *«ነገር ከስርዋ ከመነሻዋ»*፣ ጠንክሮ ከመሥራት፣ *«ያንን ገበሬ፣ያንን ዘላን» ከዝምድና፣ ‹የታፈን ወንድም አቶ አስኔዋን›* በሚል የተገለፁ ሲሆኑ እነሱም ዋና ግለሰባዊና ማኅበራዊ ማንነትን መግለጫ ነጥቦች ናቸው።

[7] ዘላን የሚለው ቃል ባለ ብዙ ከብት፣ሀብታም የሚለውን ሀሳብ የያዘ ነው፡፡

ከዚህ በኋላ "መሃል" ወይም "ጊዜ ክዋኔ" ብለን ልንጠራው በምንችለው የክዋኔ ጊዜ ከዋኙ የሚቹን ሁለንተና (ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ) ማንነት የሚገልፁ ስንኞችን እየደረደረ ይቆያል። [8] ክዋኔውን በዚህ መልኩ ሲያስኬድ ከቆዬ በኋላ ወደ መጨረሻው ሲደርስ የመዝጊያ ስንኞችን ደረደረ። የመዝጊያ ስንኞች የእሱ ክዋኔ ማለቁን የሚገልፅባቸው ሲሆኑ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ያልተሰፋ ልብስ ስሙ ነው ጣቃ፣<br>
አብቃ እያሉኝ ነው እዚህ ላይ ላብቃ፣<br>
ፈካሪ ካለህ በዚያ ተጠጋ።

ከዋኙ እነዚህ ስንኞች ያላቸው ሰዓቱ ወደስድስት ሰዓት እየደረሰ በመምጣቱ አጠቃላይ ሥርዓቱን ለመጨረስ በተፈለገበት ጊዜ ክዋኔውን አንዲጨርስ ግፊት እየተደረገበት ስለነበር ነው። በእርግጥ ስንኞቹ ከላይ ወደታች የሐሳብ መመሳሰል ባይኖርባቸውም ዋናው ቁም ነገር ሰውዬው የእሱን ክዋኔ ማቋረጡን "(መጨረሱን አይደለም)"[9] ይገልፃል።

በአጠቃላይ በባህር ዳር ከተማ፣ በሰባታሚት ከተማ በለቅሶ ዐውድ ላይ የሚከወንን የፉከራ የአከዋወን ሂደት በምንመለከትበት ጊዜ የራሱ የሆነ የአከዋወን ቅርፅ ያለውና ይህ ቅርፅ ደግሞ ትርጉም ባለው መልኩ መጀመሪያ መሃልና መጨረሻ የሚባል ክፍል ያለው መሆኑን ለማየት ተችሏል። ክዋኔ ተፈጥሯዊ የሆነ መልኩን ጠብቆ ሳይቋረጥ እንዲካሄድ በከዋኝና ታዳሚ መካከል ሥርዓታዊ ተግባቦት ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ ሁለቱም የየራሳቸውን ሚና በአግባቡ መጫወት መቻል አለባቸው። ጥናቱ በተደረገበት ክዋኔ ውስጥ የነበረው የከዋኝና ታዳሚ ሚናም እንደሚከተለው ቀርቧል።

#### *3.1.2 የከዋኝና ታዳሚ ሚና*

Bauman (1975፡95) ክዋኔ የተግባቦት ወይም ያነጋገር ስልት መሆኑን ያስረዳሉ። ከዋኙ ሥነቃሉን በሚያቀርብበት ባህል ልማዳዊ ሕግ መሰረት የሚጠበቅበትን ጥበብ እያሟላ፣ ታዳሚው ደግሞ ከሥነቃሉ የሚጠበቀውን ትውፊታዊ ውበት እያገኘ እርስ በእርስ የሚፈጥሩት ተግባቦት ሲሆን ታዳሚው የከዋኙን ባህላዊ ክህሎት ገምግሞ የሚመዝንበት እና ልምድ የሚቀያየሩበት፣ ለከወናው መፍዘዝም ሆነ መድመቅ የታዳሚው ሚና ወሳኝ የሆነበት፣ . . . ድርጊታዊ የተግባቦት ዘዴ ነው ይላሉ።

በዚህ ጥናት የተተኮረበት የፉከራ ክዋኔ የከዋኝና ታዳሚ የየራሳቸው ሚና ያለበትና በሁለቱ ተግባቦት ላይ ተመስርቶ የሚከወን ነው። ከዋኝ የሚችን ሥራ በሚገልፅበት ጊዜ፣ ታዳሚ "እውነት!" ፣ "ይል ነበር!" በማለት የተነገረውን ነገር «ትክክለኛነት» ወይም ስለሚባለው ነገር ያለውን ስምምነት ያሳያል። ከዚህ ሌላ የገንዘብ ሽልማትም ከታዳሚው የሚቀርብ የስምምነት ብሎም ከዋኙን የማትጊያ

[8] በዚህ ጊዜ የተከወኑትን የፉከራ ቃል ግጥሞች ከታች በተለያዩ ንዑኡሳን ርዕሶች የሚታዩ በመሆኑ ድግግሞሹን ለማስቀረት ስል ምን ይዘት እንደያዙ ብቻ ጠቅሸ አልፌያለሁ፡፡

[9] ክዋኔው ረጅም ሰዓት በመውሰዱ "ይበቃል" ተብሎ ያቆመ በመሆኑ ነው እንደዚህ ያልሁት

መንገድ ነው። ይሁንና የታዳሚ ግብረ መልስ ፈዘዝ ያለ ሲመስለውና ታዳሚው "ባልሁት ሐሳብ ጥርጣሬ ገብቶታል ይሆን?" ብሎ ሲያስብ ከዋኙ፡-

አይዞህ ወገኔ ልብህ አይፍራ፣
አልገባብህም ባልሠራው ሥራ።

ሲል ታዳሚውን ያረጋጋል። በከዋኝና ታዳሚ መካከል ያለውን ተግባቦት መሰረት አድርጎ «ምናልባት ከዋኙ ገበሬውን፣ ወታደር፣ ፈሪውን ጀግና አድርጎ ቢያቀርበው የታዳሚው ምላሽ ምን ይሆናል?» ለሚለው የቃለ መጠይቅ ጥያቄ መረጃ ሰጪዎች «ይህንን አይነት የጎላ ገለጻ በሚመጣበት ጊዜ ታዳሚው «ውሸት ነው!» የሚል መልስ በመስጠት ለከዋኙ መልስ እንደሚሰጡ፣ ከታዳሚዎች አንዱም የከዋኙን ሚና ነጥቆ ከዋኝ በመሆን እንደሚፈክር ገልፀዋል። (ተመስገን ፈንታሁን፣ 16/06/2011 ዓ.ም) በከዋኝና በታዳሚ መካከል ያለውን ተግባቦት ስንመረምር በአግባቡ ልናስባቸው ከሚገቡ ነገሮች አንዱ የፎክሎርን ጥበባዊነት ነው። ምክንያቱም Ben-Amos (1971) ጥበባዊነት ለፎክሎር አንዱ መገለጫ ባህርይ መሆኑን እንደሚገልፁት የፎክሎሩ ጥበባዊነት በከዋኝና ታዳሚ መካከል ያለውን ተግባቦት የሰመረ ያደርገዋል። በመሆኑም የክዋኔውን አካሄድ መሠረት አድርገን የከዋኙ የትረካ አንፃር አንድ ጥበባዊ የክዋኔ ስልት መሆኑን ለማየት ተችሏል። ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል።

### *3.1.3. የክዋኔ ጥበባዊነት በትረካ አንጻር መገለጫነት*

የትረካ አንፃር በአንድ የፈጠራ ሥራ ውስጥ ደራሲው ታዳሚውን የሚያናግርበት ድምፅ ነው (ዘሪሁን፣ 1992)። ደራሲያን በሥራዎቻቸው ውስጥ ተደራሲን በሦስት መንገድ ያናግራሉ። አንደኛው መንገድ አንደኛ መደብ የትረካ አንፃር ሲሆን ይህም በገፀባህሪነት የተሳለ አንድ ሰው "እኔ፣ እንዲህ ብዬ፣ እንደዚህ አድርጌ ." እያለ የሚተርክበት መንገድ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ አንድ ተራኪ በፈጠራ ሥራው ውስጥ የተፈጠሩ ገፀባህርያትን ድርጊት "እንዲህ አድርጎ፣ እንዲህ ብሎ ." እያለ በሦስተኛ መደብ የሚገልፅበት ነው። ሦስተኛ መደብ የትረካ አንፃር በበኩሉ ሁለት አይነት ነው። አንደኛው ሁሉን አወቅሁ ሲሆን፣ ሁለተኛው ውስን ሁሉን አወቅሁ የትረካ አንፃሮች ናቸው። በሁሉን አወቅሁ የትረካ አንፃር ተራኪው የገፀባህርውን አእምሮ እስከማገንበብ የሚደርስ ሲሆን በውስን ሁሉን አወቅሁ ተራኪው የገፀባህርይውን ድርጊት ብቻ ይገልፃል።

ቃል ግጥም በፎክሎርነቱ ጥበባዊ ነው። ጥበቡ በተለያዩ መንገዶች ይገለፃል። በዚህ ጥናት በቅርፁ (በአተራረክ አንፃሩ) ተገልጾ ተገኝቷል። በዚህ መሰረት ለትንተና በቀረቡ የፉከራ ቃል ግጥሞች ውስጥ ሁለት የትረካ አንፃሮች ተገኝተዋል። አንደኛው ፎካሪው ስለሟቹ እንዲህ ነበር እያለ በሶስተኛ መደብ የሚሰጠው ገለፃ ነው። ቀጥለው የቀረቡ ቃል ግጥሞች ጥቂት ምሳሌዎች ናቸው።

ስሞት በጥራት ፈክርልኝ ሲል የሰማሁት እኔ እኮ ነኝ፣
አደራ አልበላም በሰራው ሥራ ጥርት አድርጌ ልፎክር ነኝ፣
ያለህ ዘመዴ ሞቅ አርግልኝ፣ የጀግኔን ሥራ እኔ አውቀዋለሁ፣
ልቤን ሞልቼ እፎክራለሁ፣
ጠጥቼ ነበር ሆዴ እስኪጨንቀው፣

በልቼም ነበር ሆዴ እስኪጨንቀው፣
የአስኔዋን ሥራ እኔ ነኝ ማውቀው፤
ሲል ይናገራል።

በዚህ ቃል ግጥም የሚናገረው ፎካሪው ነው። ፎካሪው ሟቹ በሕይወት እያለ ወዳጅነት እንዳላቸው፣ ሲሞትም እንድትፈክርልኝ ያለው መሆኑን ስለዚህም ለመፎከር ሙብት (ፈቃድ) ያለው፣ እንዲሁም አደራ ያለበት መሆኑን ይገልጻል። በዚህ መልክም በየቦታው ይህንኑ የትረካ አንፃር እየተጠቀመ ሃሳቡን ይገልፃል። በሌላ ጊዜ ደግሞ ፈካሪው ሰውኛ ዘይቤን ተጠቅሞ ሟቹ ራሱ «እኔ» ብሎ እንዲናገር የሚያደርግበት ሁኔታ አለ። ለምሳሌ በቀጣይ ስንኞች ፎካሪው ፉከራው ሲጀምር ሟቹ ራሱን እንዲያስተዋውቅ ያደርገዋል። ቀጣዩ ቃል ግጥም ይህንን ያሳያል፡-

የገበሬዎች አለቃ ነኝ፣
የዘላኖችም አለቃ ነኝ፣
ካገሬ ስኖር ይቅር የለኝ፣
ሌባ ቢወስድም ማያመልጠኝ
የጀግኖች አማች፣ የነደስታ አማች፣ የእነ አበበ አማች፣ እኔ እኮ ነኝ፤

በዚህ ሀኔታ ከዋኙ በከዋኔያዊ ጥበቡ አንደኛ መደብ የትረካ አንፃር በመጠቀም ሟቹን ኅበዝ ገበሬ እንደሆነ ፣ የተትረፈረፈ ሀብት እንዳለው፣ ከሰው ጋር የማይጣላ ጠብ የማይወድ በመሆኑ የተነሳ ከሰው ጋር ለእርቅና ይቅርታ ተቀምጦ የማያውቅ መሆኑንና ጀግኖች አማቾች እንዳሉት በመግለፅ ራሱን እንዲያስተዋውቅ ያደርገዋል። በዚህ መልክ አስፈላጊ ባላቸው ቦታዎች ሟች ሲናገር ይደመጣል። ለምሳሌ በሟቹ አፍ የሚነገሩ ሆነው ከሚቀርቡ ሃሳቦች ውስጥ ቀጥሎ ሟች ለልጆቹ የሚሰጠው ምክር ይጠቀሳል።

ኧረ ግድያን አትታከኩ፣ ኧረ መሃላን አትታከኩ፣ ኧረ ክደሽን አትታከኩ
ከባድማችሁ ልጅ እንድትተኩ
እኔ አባታችሁ ብገድል ኑሮማ፣ እኔ አጎታችሁ ብምል ኑሮማ
የት ይገኝ ነበር ይኸ ባድማ

በእነዚህ ስንኞች ሟች የራሱንና የእህት ወንድም ልጆቹን ሕይወት በአስተማማኝ ሁኔታ እንዲቀጥል ሰው መግደል፣ መሃላ፣ ክህደት መፈፀም እንደሌለባቸው ይመክራል። አትግደል ሃይማኖታዊ ትዕዛዝ ነው፣ መሃላ፣ በሁለት ሰዎች መካከል የሚደረግ ባህላዊ የመተማመኛ ሰነድ ነው። ይሁንና በማኅበረሰቡ ዘንድ ግድ ካልሆነ በስተቀር መማልም ሆነ ማስማል አይመከርም። አንድን ጉዳይ፣ አድርጎ «አላደረግሁም» ሲል የማለ ሰው ልጅ አይተካም፣ መሃላው እስከ ልጅ ልጅ የሚተርፍ መጥፎ ነገር ይጠራል ተብሎ የሚታመን ሲሆን አንድን ነገር ያላደረገን ሰው ማስማልም በአስማዩ ላይ ርግማንን ያመጣል ተብሎ ይፈራል (አለም መኮንን፣ አስማሩ ፈንታሁን፣ 16/06/2011 ዓ.ም)። ይህ ማኅበራዊና ባህላዊ እምነት ነው። ስለዚህ ከዋኙ ሟች በሕይወት ሳለ የነበረውን የተደላደለ ሕይወት ማሳያ አድርጎ ስለ መሃላ፣ ክህደትንና ግድያ ማኅበረሰቡ ያኖረውን እሴትና ደንብ

ይሰብካል። ይህ እና ሌሎች በፉከራው የሚነሱ ዕውቀቶች በእርግጥ የማኅበረሰቡ የጋራ እሴት መሆናቸውን ደግሞ በክዋኔው ውስጥ ያለው የከዋኝና ታዳሚ በየሚናቸው የሚፈፅሙት ክወና የሚፈጥረውን ህብር ይገለፃል።

### 3.2. የጀግና ብያኔ በለቅሶ ዐውድ ላይ በሚከወን የፉከራ ቃል ግጥሞች ይዘት ውስጥ

ማንኛውም ማኅበረሰብ በራሱ መስፈሪያ ሰፍሮ ጀግና ሲል የሚሾማቸው ግለሰቦች አሉት። እነዚህ ግለሰቦች የሚለኩበት መስፈሪያ እሴት ይባላል። እሴቶች፣ በማኅበረሰብ ህይወት ውስጥ ጠቃሚ የሆኑ ሃሳቦችን የሚይዙና ሌሎችን የባህል ክፍሎች የሚመሩ ናቸው። እሴቶች በደንቦች ይጠበቃሉ። ደንቦችአንድ ህዝብ ሊኖረው ይገባል ተብለው የሚገመቱ ስርዓቶችን ይይዛሉ። እነዚህ ግምቶች እያንዳንዱ ማኅበረሰብ ደንብ እንዲያከብር የማስገደድ ባህርይ አላቸው። የሚያስገድዱት ልማዶች ደግሞ ምንም እንኳ ያልተጻፉ ቢሆኑም የሕግነት ደረጃ አላቸው። ትዕምርቶች የሚባሉት ደግሞ እሴቶችና ደንቦች የሚፈጥሯቸው የማኅበረሰብ መለያ ናቸው (Luigi 2003)።

መረጃዎች እንደሚገልፁት ማኅበረሰብ የራሱን ቅርፅ አስጠብቆ ለመኖርና ህልውናውን ለማስቀጠል እሴቶችና ደንቦች የማኅበሩ አባል ለሆኑ ግለሰቦች ያስተምራል፣ በግለሰቦች እንዳይጣሱ ይጠብቃቸዋል፣ እንዳይጠፉ ይቆጣጠራል፣ ለማጥፋት የሚሞክሩትን ይቀጣል። በአንፃሩ የሚያከብሩና የሚጠብቁ ግለሰቦችን ደግሞ ይሸልማል። ብዙ ጊዜም ግለሰቦችን ከሌላው ማኅበረሰብ ለይቶ ያከብራቸዋል ጀግና ብሎም ይጠራቸዋል (Bascom 1965) ።

ማንኛውም ማኅበረሰብ ጀግና ሲል የሚሰይመው ግለሰብ ይኖራል። ይህ ግለሰብ ማኅበረሰቡ ይሁነኝ ብሎ ባዘጋጀው ሥርዓት ውስጥ የራሱ መገለጫ የሆነውን እሴትና ደንብ ጠብቆና አክብሮ የሚኖር ሰው ነው። Luigi (2003) እንደሚሉት ጀግና ከማኅበራዊ ሕይወትና ማኅበረሰቡ ካለበት ተጨባጭ ሁኔታ የሚፈጠር ነው። ይህ በመሆኑ በአንድ ማኅበረሰብ ለጀግንነት የሚሰጠው የጀግንነት መሰፈሪያ ልክ ለሌላው ማኅበረሰብ ላያገለግል ይችላል። ይልቁንም የግለሰቡ ጀግንነት ከማኅበረሰቡ ማንነት የሚቀዳ ነው። በዚህም መሰረት ጦረኛ በሆነ ማኅበረሰብ ውስጥ ተኩሶ የማይስት፣ ጥሩ የጦር አመራር ብቃት ያለው ሰው ጀግና ሲባል በግብርና በሚተዳደር ማኅበረሰብ ውስጥ ደግሞ ያለ ድካም የሚያርስ፣ ብዙና ጥሩ የሚያመርት ሰው ጀግና ሊሰኝ ይችላል።

በባህር ዳርና በዙሪያዋ የሚገኙ ድሽት፣ ጎርደማ፣ ሰባታሚት የሚባሉ አካባቢዎች የሚኖሩ ማኅበረሰቦች የመተዳደሪያ መንገዳቸው ግብርና በተለይም እርሻ ነው። በመሆኑም በእነዚህ ቦታዎች በሚኖሩ ማኅበረሰቦች ዘንድ ጎበዝ ገበሬ ይወደሳል። ሰነፍ ገበሬ ደግሞ ይወቀሳል። አካባቢዎች ከግብርና ጋር ተያይዞም ሆነ በሌሎች ማኅበራዊ ሕይወቶች መልካም ሲሉ የተቀበሏቸውና ክፉ ሲሉ የሚነቅፏቸው ባህርያት አሉ (መሰንበት አስማረ፣ 16/06/2011 ዓ. ም)። በማኅበረሰቦች ውስጥ እነዚህን ባህርያት ክፉዎችን በክፉነት በጎዎችን በበጎነት ተቀብሎ የሚኖር ማኅበረሰብ ጀግና ነው። ይህ ጀግና በሕይወት እያለም ይሁን ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቶ በተለያዩ መንገዶች ይወደሳል። ውዳሴው ከሚቀርብባቸው መንገዶች አንዱ ፉከራ ነው።

### 3.3. በፉከራዎች ውስጥ የተንፀባረቁ ዋና ዋና የጀግና መገለጫ እሴቶች

በለቅሶው ክዋኔ ወቅት በምልከታ፣እንዲሁም በክዋኔውና ከክዋኔው ውጪ በቃለመጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን በመመርመር በፉከራው ውስጥ የቀረቡና በከዋኙ ቡድን የጀግንነት ማሳያ ሆነው

የሚታወቁ፣ ማኅበረሰቡ ከጀግና የሚጠብቃቸው መልካም እሴቶችና፣ ማኅበረሰቡ ከጀግና የማይጠብቃቸው እኩይ ምግባሮች ለመለየት ተችሏል። መልካም እሴቶች፤ ጠንካራ ሠራተኛነት፣ ባለሀብትነት፣ ቤተሰብን መውደድ፣ ትዳርን ማክበር፣ በሽምግልና ተግባር መሳተፍ፣ እንግዳ ተቀባይት፣ መንፈሳዊነት፣ የሁለገብ እውቀት ባለቤት መሆን ሲሆኑ እኩይ ምግባሮች ደግሞ ስርቆት፣ ስንፍናን፣ መሀላን መፀየፍ፣ የሚሉ ናቸው። ዝርዝራቸው ቀጥሎ ቀርቧል፡-

### 3.3.1. መልካም እሴቶች

#### *1. ጠንካራ ሠራተኛነት*

ሰባታሚትን ጨምሮ በባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ የሚገኙ ቀበሌዎች የኢኮኖሚ መሰረት በአብዛኛው ግብርና ነው። የግብርናው አይነትም እርሻና ከብት እርባታን ጠቅልሎ የያዘ ሲሆን በእርሻ ሥራ በቆሎ፣ ጤፍ፣ በሎቄ፣ ጓያ፣ ሽንብራ፣ ቃሪያ፣ ቀይ ሽንኩርት፣ ቲማቲም፣ ማንጎ፣ አቦካዶ፣ ፓፓያ፣ ዘይቱናና ሸንኮራ አገዳ፣ ይመረታሉ። በአካባቢው ማኅበረሰብ ዘንድ ከእርሻ ሥራ ባሻገር እንስሳትን በማርባት ለምግብነትና ለሌሎች አገልግሎቶች መጠቀም የተለመደ ነው። የጋማ ከብቶች፣ የቀንድ ከብቶችንና ዶሮዎች በአካባቢው የሚረቡ የቤት እንስሳት ናቸው (ባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ግብርና ፅ/ቤት፣ 1999)። በመሆኑም ለጥናቱ ተብለው የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት የግብርና ሥራን በአግባቡና በጊዜው መሥራት፣ ጥሩ ውጤትና ምርት ማግኘት ጀግና አስብሎ የሚያስመሰግን አንድ እሴት ነው። ቀጣዩ የፉከራ ቃል ግጥም ይህንን ያሳያል።

*አይዞህ ወገኔ ልብህ አይፍራ፣አልገባብህም ባልሠራው ሥራ*
*የጀግኖች ወንድም የእነዚያ ሁላ፣ ሌት ተቀን ብሎ ሰርቶ ሚበላ*
*ጅሉ ገበሬ ሽል አይቶ አይዘራ፣ ደህና ቤት ያለው እንግዳ አይፈራ።*
*አቶ አስናቀ ሺጋው ግንባራም፣ አለው ችጋርን ተመለስ አራም።*
*ችጋር ሚባለው ከደጁ ደርሶ፣አላስገባውም ሄደ መልሶ፣*
*ችጋር ሚባለው ከፊቴ መጥቶ፣ ትክ ብሎ ቢያየኝ ትክ ብዬ አየሁት*
*ምን ሰው ነህ ቢለኝ አስኔ ነኝ አልሁት፣አስገባኝ አለኝ ተመለስ አልሁት።*
*እኔም ቀን ከሌት ነበር ያረስሁት፣ምንም ከደጄ አላስደረስሁት*
*ወደ ሰነፉ ከዚያ መለስሁት*
*ወንፊል አልገጥምም ከሰነፍ ጋር፣ ወበር አልገጥምም ከሰነፍ ጋራ*
*ያስቀርብኛል ያመት አዝመራ፣ መንደር ለመንደር ወሬ ሲያወራ።*
*ሰነፍ ሚወደው ዳስ አመት በዓል ነው*
*ኧረ አንተ ሰነፍ ዳስና አመት በዓል ምትወድ ለምንድን ነው*
*ገትረው ከሰሩ ቤት አመት ባል ነው። «አለ አስናቀው! »*

ከላይ በቀረቡት ስንኞች ፎካሪው አስቀድሞ ስለሚቹ ማንነት ላስረዳችሁ ስለሆነ ተዘጋጁ በሚል መንፈስ ሚቹን በትክክለኛ ማንነቱ ሊገልፀው እንደተዘጋጀ መግለጫ ይሰጣል። ከዚያ በኋላም ከዋኙ በሦስተኛ መደብ የትረካ አንፃር (በራሱ ምስክርነት) ሚቹ በህይወት ዘመኑ ምንአይነት ጠንካራ ሠራተኛ እንደነበር ይገልጻል። ከዚህ ባሻገርም የሰጠውን ገለፃ ታማኝነት ከፍ ለማድረግ በሚመስል

ሁኔታ አንደኛ መደብ የትረካ አንፃር ተጠቅሞ ሟችን እንዲናገር በማድረግ ሀሳቡን ያጠናክራል። «እኔም ቀን ከሌት ነበር ያረስሁት» በሚለው ስንኝ ተገልፆ እንደሚታየው ሟቹ ለድካም ቦታ የሌለው ጠንካራ ገበሬ ነበር። ችግር እንዲደርስበት አይፈልግም፣ ከሰነፍ ጋር ጓደኝነት የለውም። መርሁ ጠንክረው ከሰሩ ሁልጊዜ ደስታ ነው የሚል ነው። ይህ ማንነቱም ሟቹ የተመሰገነበትና የታወቀበት መሆኑን እሱ በተናገረው ሀሳብም መስማማቱን « አለ አስናቀው!» (የሟቹ ስም) ሲል ግራ ቀኙን እየቃኘ ታዳሚውን ይጠይቃል። ታዳሚውም በተራው «እውነት ነው! » ሲል ሀሳቡን ያፀድቀዋል። በዚም ማኅበረሰቡ ለጠንካራ ሠራተኛ ያለውን ከፍ ያለ ቦታ ያሳያል።

በፉከራ ቃል ግጥሞቹ ከቀረቡ ግለሰብ ጀግና ከሚያስብሉ ሀሳቦች ውስጥ የተገኘው ሌላው ነጥብ «ሀብታም» መሆን ሲሆን ለዚህ ሀብታምነት ግን ምንጩ ጠንክሮ መሥራት ነው የሚል ነው። ቀጥሎ የቀረቡት የፉከራ ስንኞች ይህንን ሀሳብ የሚያሳዩ ናቸው።

### *2. ሀብታምነት (ጠንክሮ በመስራት የተገኘ)*

የሆነ፣ ልጅ የለለው ጣጣ፣ሃምሌ ነሃሴ ችግር ቢመጣ
አይገባ ብድር አይገባ አራጣ፣ነጮን ሽጦ ነው ብር የሚያመጣ
የአጅሬ ልጆች መታደላቸው፣አንድ ቀን ማጫው አይጎድልባቸው።
አምስቱን ጊደር ነው ሚሰጣቸው፣ አምስቱን ወይፈን ነው ሚሰጣቸው
ቀረ እንጅ እንግዲህ ሲሞትባቸው። ልበል?
ኧረ ያ ጊደር የማን የማን ነው? ፣ የሽጋው ዘላን[10] የአቶ አስናቀው ነው!
ኧረ ያ ቡኸር የማን የማን ነው? ፣ የሽጋው ዘላን የአቶ አስናቀ ነው!
ያን ሁሉ ጊደር ምን ሊያደርገው ነው ዘላንነቱ የዘር ሆኖ ነው።
ያ ሁሉ ወይፈን የማን የማን ነው? ፣ የሽጋው ገበሬ የአቶ አስናቀው ነው!
ያ ሁሉ ወይፈን ቀንበር ያልወጣው ምንድን ሆኖ ነው?
በሬው በዝቶበት ቸለል ብሎት ነው! ልበለው?
እየው ያ ክምር የማን የማን ነው? ፣ የዚያ ገበሬ የአቶ አስናቀው ነው!
*ማያበራየው ምንድን ሆኖ ነው? ፣ ጎታው ሞልቶበት ቸለል ብሎት ነው!*

ከመረጃዎች መገንዘብ እንደሚቻለው ሟች በማኅበረሰቡ ውስጥ ከሚያስከብሩትና አንቱ ካሰኙት መገለጫዎቹ ውስጥ ሀብታምነቱ አንዱ ነው። ሟቹ ብዙ አምራች ነው። ብዙ የቤት እንስሳት (ላምና በሬዎች) አሉት። አስቀድሞ እንደተገለጸው የማኅበረሰቡ መተዳደሪያ ግብርና በመሆኑ ሀብቱ የሚለካው በእርሻ ምርትና በእንስሳት ሀብት ብዛቱ ነው። ይህ ዝናው የሚነገርለት ሟችም ከብዛታቸው የተነሳ ለእርሻ ተራ ያልደረሳቸው ወይፈኖች፣ ከመትረፍረፋቸው የተነሳ ያልተበራዩ ክምሮች ባለቤት ነበር። ልጆቹን ሲድር ለመተዳደሪያ የሚሰጠው የከብት ብዛት ከአካባቢው ማኅበረሰብ በቁጥር የሚበልጥ ነው። በአጠቃላይ በቃል ግጥሞች ሟቹ ጠንክሮ በመሥራት ባገኘው ሀብት የተነሳ በማኅበረሰቡ ዘንድ ከፍ ያለ ማኅበራዊ ደረጃ ይዞ የቆዬ ሰው መሆኑን ለመረዳት

10 በአካባቢው ዘዬ ዘላን የሚለው ቃል፣ብዙ ከብቶች ያሉትን ሰው ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል ነው (ውዴ እንዳለው፣ 16/05/2011 ዓ.ም)

ይቻላል። ሌላው የሚቹን ጀግንነት ከሚያሳዩ ነገሮች አንዱ ለቤተሰብ ያለው ፍቅር ነው። ቀጥለው የቀረቡት ቃል ግጥሞች ይህንን ያሳያሉ።

***3. የቤተሰብ ፍቅር***

የሴቶች ሊቅ ናት ያገባት ሚስቱ
ኧረ ካሳነሽ የእኔ ቦልካታ፣ ባል አትነዘንዝ ጧትና ማታ
ልጅ አትቆነጥጥ አታንገላታ፣ ከጎረቤት ጋር ስትኖር ተስማምታ
በደሮ ጩኸት ሌሊት ተነስታ፣ ደም የመሰለ ቡንዋን አፍልታ
ያንን ጨብጠው ካቶ አስናቀ ጋር የነበር ጨወት የነበር ፌሽታ
የስምዋ ማማር ዛሬ እንኳን ሙታ። ልበላት?

ቃል ግጥሙ ሚቹንና ባለቤቱን ያነሳል። በግጥሙ ውስጥ በባልና ሚስት መካከል ፍቅር የነበረ መሆኑን ያሳያል። ይህ የባልና ሚስት ስም ግን የሐሳብ ማሳያ ነው። ምክንያቱም በግጥሙ ውስጥ ለባልና ሚስቱ ፍቅር መሰረቱ የሴቷ ባህርይና ምግባር ነው። ሴቷ ፀባየ ጥሩ፣ ብሎም መልከ መልካም ናት። ሳቅ ጨዋታ መውደዷንና ዘና ያለ ፀባይ ያላት መሆኗን ለመግለፅ «ቦልካታ» ይላታል። የጠባይዋን ማማር፣ ከባልዋ ጋር ጭቅጭቅ ባለመፍጠርዋ፣ ልጆችን ባለመግረፍዋ (ባለመቆንጠጥዋ)፣ ከጎረቤት ባለመጣላትዋ፣ ታታሪ ሠራተኛ በመሆንዋ የሚገለፅ ነው። እነዚህ ጉዳዮች ደግሞ የአንዲት ሴት ባህርያት ብቻ ሳይሆኑ ማኅበረሰቡ አንዲት ሚስት ልትሆን ይገባል ሲል ካበጃቸው እሴቶች ውስጥ የሚጠቀሱ ነጥቦች ናቸው። እንግዲህ አንዲህ አይነት ሚስት ያለችው ማንም ወንድ ስኬታማና ጀግና መሆኑ ሃቅ ነው። «ከእያንዳንዱ ስኬታማ ወንድ ጀርባ አንዲት ጠንካራ ሴት አለች» ነውና። በመሆኑም መልካም ትዳር የማኅበረሰብ እሴት ነውና መልካም ትዳር እንዴት ይገነባል ለሚለውም ማኅበረሰብ ደንብ አለው። ቀጥሎ የቀረበው ንዑስ ርዕስ ይህንን ያሳያል። ይህንን ደንብም ፈካሪው በሚከተለው ግጥም ይፈክረዋል።

## 4. ትዳርን ማክበር

በምልከታ እንዲሁም በቃለመጠይቅ (አለም መኮንን፣ 13/06/2011) የተገኙ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በተጠኘው ማኅበረሰብ ዘንድ ትዳር ጥብቅ መሠረት ያለው ማኅበራዊ ተቋምነው። ልጅ ወልዶ በአግባቡ አሳድጎ ለትዳር ማብቃት ማንኛውም ወላጅ የሚመኘውና ከትውልድ ትውልድ ሲሸጋገር የኖረ እሴት ነው። በመሆኑም ማንኛውም ቤተሰብ ወንድም ይሁን ሴት ልጁን ትዳር ለማሲያዝ ሲፈልግ ከማን ጋር ይሁን የሚለው ጥያቄ ትልቅ ትኩረት የሚፈልግ ነው። በፉከራ ቃል ግጥሞቹ የተገለጹት ግለሰብ፣ ትዳርን የማክበር ታሪክ ያላቸው ናቸው። ትዳርን ማክበር ደግሞ ጀግና ከሚያስብሉ ሀሳቦች ውስጥ አንድ መስፈርት ነው። ቀጥሎ የቀረበው መረጃ ይህንን ይጠቁማል።

በዘራቸው፣ እንደተረቡ [11]ገበሬ ናቸው
እንደተረቡ ዘላኖች ናቸው፣ እንደተረቡ ዳኞዎች ናቸው
ጉልበት ሳያጡ አይ ቸሎታቸው፣ በዚህ አይደለ ፈጣሪ አምላክስ የሚወዳቸው
በጠዋት በጠዋት የሚጠራቸው፣
የዚህን ቤት ሰዎች አትጋቧቸው፣ እነአስናቀውን አትጋቧቸው
ጉልበት ነው እንጅ ዕድሜም የላቸው።
ኸረ ባስበው ተሳስቻለሁ ግና መጋባት ከእነሱ ቤት ነው
የደህናው ግቢ በአመትባል ቁጥር ሳቅ ጨዋታ ነው፡
የጅሉስ ግቢ እየተጣላ ሽምግልና ነው።
በተለይ ደግሞ ሴት እህቶቼ ባል ስታገቡ ከእነሱ ቤት ነው
ሻል ሻል ያለው እንዲወለድ ነው
ከላም ቢሰዱት እንዲያረባ ነው
ዳኛ ቢያደርጉት ልክ እንዲፈርድ ነው፣ እንዲመራ ነው
እርሻም ቢሰዱት እንዲያመርት ነው።
የጅሉ ሰው ልጅ እዚያው ማልቀስ ነው። አይደለም ያለ?

በምልከታ እንዲሁም በቃለመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ጋብቻ በማህረሰቡ ዘንድ ትልቅ ዋጋ ከሚሰጣቸው እሴቶች ውስጥ አንዱ ነው። የጋብቻን ምንነት አስመልክቶ በርካታ ምሁራንና የተለያዩ ሰነዶች የተለያዩ ብያኔዎችን ይሰጣሉ። ለምሳሌ የStewart (2006) እና Peter (2011)ን ብያኔ ወስደን ስናይ ጋብቻ በመላው ዓለም የሚፈጸምና አፈጻጸሙ እንደየባህሉ የሚለያይ የሰው ልጅን ህይወትና ባህል ለማስቀጠል መሰረት የሆነውን ቤተሰብ ለመመስረት እንዲሁም ህጻናትን በሕጋዊ መንገድ ከሁለቱ ወላጆች ለማፍራት በአንድ ነጻ ወንድና በአንድ ነጻ ሴት መካከል የሚደረግ ግንኙነትና ስምምነት ሲሆን ግንኙነቱ መደበኛና በማኅበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው የሚደረግበት ማህበራዊ ተቋም መሆኑን እንገነዘባለን። በተጠኚው ማኅበረሰብ ጋብቻ ክብር ያለው ተቋም ነው። በዋነኛነት በማኅበረቡ ዘንድ ጋብቻ የሚፈፀመው በወላጆችና ዘመዶች አመቻችነት ሲሆን ሁለቱ ወገኖች ተጋቢዎችን በጋብቻ ለማስተሳሰር አስቀድሞ ሴቷንም ሆነ ወንዱን ለመገምገም ሲባል ያዘጋጇቸውና ከትውልድ ትውልድ ሲወራረሱ የኖሩ መስፈርቶች አሉ። በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች እንደሚያሳዩትም ጠንካራ ሠራተኛነት፣ ሰላም መውደድ፣ ቃልን አለማጠፍ (የሀሰት ንግግር የማይናገር) ወዘተ የሚሉት ሀሳቦች በተጋቢዎች ዘንድ ጋብቻውን ለመፈፀምና ላለመፈፀም የሚያገለግሉ መስፈርቶች ናቸው። ቀጣዩ የቃል መረጃ ከላይ የቀረበውን ሀሳብ የሚደግፍ ነው።

> እህ፣ ያው ለወንድ ልጆቻችን ሚስት ስናጭ፣ የማን ልጅ ናት፣ እናትዋ ውለቷ ምንድን ነው? ባህርይዋስ እንላለን መቼስ «እናቲቱን አይተህ ልጅቱን አግባ አይደል?» ሙያ አላት ወይ፣ ከሰው አትጣላም ወይ፣ ጠባይዋ መልክዋ እንላለን። ደሞ ባባቷ ግድም አባቷ ኀበዝ አራሽ ነውን፣ተሰው ጥሩ ተግባቦት አለውን? ጥሩ ንሮ ይኖራል? ሰው ያከብራል፣ እሱስ በንበቴው በማህበሩ

[11] «ረባ» ከሚለው ግስ የወጣ ቃል ነው፡፡ ከስር መሰረታቸው የሚል ትርጉም አለው፡፡

ተሰው ስምም ነው? ላጣ ይሰጣል? ለተቸገረ ያበድራል? እንላለን (ይሙኑ እውነቴ፣ 13/06/2011፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሰባታሚት)።

መረጃው ጋብቻ የራሱ መልክና ሥርዓት ያለው እሴት መሆኑን ያሳያል። ይህ እሴትም ከነክብሩና ሥርዓቱ እንዲቀጥል አስቀድሞ በተዘጋጁ መስፈርቶች ተመርምሮ እንደሚገባበት ከመረጃው መገንዘብ ይቻላል። ከላይ የቀረቡ ስንኞቹ ትዳር ትልቅ ነገር መሆኑን ይገልፃሉ። በመሆኑም በድንገት ተመስርቶ፣ በድንገት ሊፈርስ እንደማይገባው ያትታሉ። ለዚህ ማሳያ የሚቹ ሕይወት ይጠቀሳል። የትዳር ሕይወት ምን ሊመስል እንደሚገባው የሰውየው ሕይወት ማሳያ ሆኖ ቀርቧል። መረጃዎች እንደሚሉት ሚቹ፣ እንደ ዳኝነነት፣ ግብርና፣ ማኅበራዊ ሕይወት ባሉ የሕይወት መልኮች ጥሩ ደረጃ አለው። ጋብቻ መፈፀም ያለበት ይህንን ከመሰለ ሰውና ከቤተሰቡ ጋር ሊሆን ይገባል። ይህንን ከመሰለ ሰው ጋር የተገነባ ጋብቻ ስኬታማ ነው።

ከዚህ ባሻገር በፉከራ ግጥሞች ጋብቻ መፍረስ የሌለበት ተቋም ነው የሚለውን የማኅበረሰብ ደንብም ከዋኙ በሚቹ አፍ (በአንደኛ መደብ የትረካ አንፃር) እንደሚከተለው ያቀርባል።

ሴት ልጆች አሉት በየሃገሩ፣ ሴት እህቶች አሉት በየሃገሩ
የያዙ ትዳር የያዙ ቤት
መቼም ቤት ይዞ አይቀርምና ከቀን አንድ ቀን ከባለቤት ጋር መገጫጨት
ኧረ ባብዬ ኧረ ተጣላሁ ና ድረስልኝ ብትል ሳር ሚጥጣ፣ ማተብዋን ቆርጣ ስትልክበት
ቁጭም አላለ ሄደ በጠዋት ሊያፋታም አይደል ሊያመካክራት
እንዲያ መካከሮ ሲሄድ ጥሏት፣ ያንቺው መጎጅያ ለእኔ አይጠፉኝም
በጉልበት ቢሆን ከእኛ ላይበልጥ፣ በሀጉም ቢሆን ከእኛ ላይበልጥ
በእጅሽ ይዘሽኝ ምትወቃቅሽኝ፣ መከሬው ልሂድ ተይ ተይ ታገሽኝ
ቤት ነው ማሰራሽ አመካክሬ ከባልሽ ጋራ
ቤት አላፈርስም ደግሞ እንደሰይጣን ደግሞ እንዳሞራ። አይደለም ያለ የእነዚያ ወንድም?

ከመረጃዎች ማየት እንደሚቻለው ትዳር ምንም እንኳን ማኅበረሰቡ ይሁነኝ ብሎ ባዘጋጃቸው መስፈርች ተፈትኖ የሚጀመር ቢሆንም ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ በእውቀት ሊመራ ይገባዋል። ይህንን የመሰለ ዕውቀት ያለው ሰውም የጋብቻን ኀልውና አስጠብቆ ቤተሰብ እንዳይበተን ማድረግ የቻለ በመሆኑ ጀግና ነው። ለምሳሌ ከላይ የቀረቡት ስንኞች እንደሚሉት ሚቹ በኃብት፣በዕውቀት፣ በጉልበት ከልጁ ባል ይበልጣል። ይሁንና ይህንን ጉልበቱን ተመክቶ ምንም አላደረገውም። ልጁንም ስለበደለሽ ትዳርሽን ፍቺና ነይ የሚል መልስ አይሰጣትም። ይልቁን ያወያያቸዋል። ምክንያቱም ትዳርን ማፍረስ እኩይነት ነው። ይህም ማኅበረሰብ በትዳር መፍረስ ምክንያት የሚከሰትን ማኅበራዊ ቀውስ ግምት ውስጥ በማስገባት ትዳር እንዳይፈርስ ከሚያደርጋቸው ጥረቶች ውስጥ አንዱ ነው። ይህንን ጥረት አውቆ የሚፈፅመው ግለሰብም ጀግና ይባላል።

መረጃ ሰጪዎች እንደሚገልፁት አንድ ግለሰብ በአንድ አካባቢ (መንደር) ሲኖር ኀልውናው ከሚረጋገጥባቸው ሁኔታዎች ውስጥ የተጣላን ማስታረቅ፣ ደግሶ ማብላት፣ እንግዳ መቀበል የታወቁ እሴቶች ናቸው። እነዚህን እሴቶች ፈካሪው እንደሚከተለው ይገልፃቸዋል።

## 5. የተጣላን ማስታረቅ፣ (ሽምግልና)

የተጣላን ሽምግሎ ማስታረቅ አንድ የጀግና መገለጫ እሴት መሆኑን ቀጥለው የቀረቡ ስንኞች እንደሚከተለው ገልፀውታል።

እሁድ ቅዳሜ ሰንበት ሲመጣ፣ ልብሱን አጣጥቦ ከደብር ወጣ
ደብር አርፍዶ ቤቱን ሲመጣ፣ ሁለቱ አልፎ ሃጅ በፊቱ መጣ
ተጣልተውበት በብር አራጣ
እነዚያን ሰድቦ አስታርቆ መጣ
የአቶ ሆነ ልጅ የሌለው ጣጣ

ከላይ የቀረቡ ስንኞች እንደሚገልፁት ሟቹ፣ የተጣሉ ሰዎችን የማስታረቅ ችሎታ ያለው ሰው ነው። የችሎታው ልክ በድንገት ያገኛቸውን ሰዎች ሳይቀር የጠባቸው ምክንያት ገንዘብ ቢሆንም እንኳን (ከማኅበረሰቡ ልማድ የተገኘ መረጃ እንደሚለው በገንዘብ የሚመጣ ጠብ ከባድ ነው) ለጀግናው አልከበደውም። *«የአቶ ሆነ ልጅ የሌለው ጣጣ » የሚለው ስንኝ እንደሚጠቁመው ሟቹ ይህንን ለማድረግ በቂ እና የታመነ ነው።* ሌላው የጀግናው የጀግንነት መለኪያ እንግዳን በምቾት ማስተናገድ መቻል ነው። ቀጣዩ መረጃ ይህንን ይላል።

## 6. እንግዳ ተቀባይነት

ጥናቱ በተካሄደበት ማኅበረሰብ እንግዳን መቀበል አንድ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ እና ማኅበራዊ እሴት ነው። ይህን እሴት በደስታ እና በልግስና መፈፀም የአንድ ቤተሰብ መከበሪያ ሲሆን የአባወራው ደግሞ የጀግንነቱ መገለጫ መሆኑን ቀጥሎ የቀረቡ ስንኞች ያሳያሉ።

የሴቶች ሊቅ ናት ወ/ሮ ካሳነሽ የጀግኔ ምሽቱ
የሴቶች ሊቅ ናት አስኔዋ ምሽቱ
የተሟላ ነው የአስኔዋ ቤቱ
እንግዳ ሲመጣ ከትከት ትልና ወጥታ ለእለቱ
ጥልቅ ትልና ከማድቤቱ፣ ዙሩን አዙራ በግሬራይቱ
የኪሎ ግማሽ ፈልታ ቡኒቱ፣ በጥሩ ወጭት ቋንጣ ወጢቱ
መለል ያለ ነው ገንቦው አንገቱ፣ መጠጫው አምሳ ሲሆን ብዛቱ
እያመጣች ያን በፊት በፊቱ
ያን አስጨብጦ አሞራው አስኔ ማር ነው ጨወቱ
አያውካካነ ሳይታወቀን ይነጋል ሌቱ።

በዚህ ቃል ግጥም ጀግናው በእንግዳ መስተንግዶ ያለውን ችሎታ አቅም ማየት ይቻላል። አስቀድሞ የአካባቢው ብሂል «ከፍትፍቱ፣ ፊቱ» እንደሚለው የጀግናው ሚስት፤ እንግዳ ወደ ቤትዋ ሲመጣ በሳቅና በመልካም ፊት ትቀበለዋለች፤ ከዚያም የተትረፈረፈ ድግስ አቅርባ እንግዳዋን ትጋብዛለች። ባልም በበኩሉ ለእንግዶች ስሜት የተመቹ ጨዋታዎችን እያመጣ፤ እንግዶች ያለድካምና መሰልቸት እንዲጫወቱ ያደርጋል። ይህ በባልና ሚስት መግባባት የሚከወን የእንግዳ አቀባበልም ለግለሰቡ የጀግንነት መለኪያ ሆኖ ተነስቷል።

እስካሁን በቀረቡ ቃል ግጥሞች ግለሰቡ በምድራዊ ሕይወቱ ያሉት ባህርያቱ የተገለጹ ሲሆን ማኅበረሰቡ የክርስትና እምነት ተከታይ እንደመሆኑም ከሞት በኋላ ሕይወት አለ ብሎ የሚያምን ነው። ጀግና የምድራዊ ሕይወቱን ብቻ ሳይሆን ሰማያዊ ሕይወቱንም ያስተካክላል የሚለውን እሳቤውን በቀጣዩ ርዕስ ሥር የቀረቡ ስንኞች ያሳያሉ።

## 7. ኩነኔን ማሰብ (መንፈሳዊነት)

በቃለመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ተጠኝው ማኅበረሰብ የተራበን ማብላት፣ የተቸገረን መርዳት ፅድቅን ያስገኙናል ሲል ከሚከውናቸው ተግባራት ውስጥ የሚጠቀሱ ተግባራት የሚመደቡ ናቸው። እነዚህን ተግባራት ሳይሰለቹ በልግስና መፈፀም አንድን ሰው በጀግንነት የሚያስጠሩት መሆኑንም ቀጥለው የቀረቡ የፉከራ ግጥሞች ያሳያሉ፡-

ጠላ ለሚሉሽ ጠላ ስጫቸው
እርጎ ለሚሉት እርጎ ስጫቸው
በሽምግልናው እናስታርቃቸው
ብር ለፈለጉት ብር ስጫቸው
ኋላም ብድሩን አትጠይቂያቸው
በላይኛው ቤት ምስክር ናቸው
ለነፍሳችን ነው የሰጠናቸው ከእኛ ጋር ለፍርድ ሚቀርቡ ናቸው አይደለም ያለ የእነዚያ ወንድም?
እውነት ነው!

ስንኞች የተቸገረን መርዳት መንግስተ ሰማያትን መውረሻ መንገድ ነው ይላሉ። ጀግናውም ይህንን ከማኅበረሰቡ ሃይማኖት የተቀዳ እውቀት መሰረት አድርጎ ሀብቱን ለሰማያዊ ህይወቱ ማደላደያ ሲጠቀምበት እንደኖረ ተገልጧል።

ከዚህ ባሻገር ማኅበረሰቡ መልካም የሚላቸው እሴቶች እንዳሉት ሁሉ የማይወዳቸው እንዳይደረጉ የሚፈልጋቸውና እኩይ የሚላቸው፣ በተቻለው መጠንም እንዳይከሰቱ የሚጠብቃቸው ጀግናውም የሚፀየፋቸው ባህርያትም አሉት። ማሳያዎች ቀጥሎ ቀርበዋል።

### *3.3.2 ማኅበረሰቡ ከጀግና የማይጠብቃቸው እኩይ ምግባሮች*

Luigi (2003) እንደሚሉት ጀግኖች የማኅበረሰባቸው ሞራላዊ እሴት የሚገለፅባቸው እና ትምህርት የሚሰጥባቸው አርዕያዎች ናቸው። ማኅበረሰብ ጀግኖችን ከእሴቶቹ ይሠራቸዋል። አንድ ግለሰብም መልካም እሴቶችን በማድረጉ ብቻ ሳይሆን እኩዮችን በመታገሉ ጀግና ይባላል። ለምሳሌ ስርቆት፣ ስንፍና፣ ክህደት፣ መሃላና ሰው መግደል በዚህ ክዋኔ ውስጥ የተጠቀሱ ማኅበረሰቡም ሆነ ጀግናው የሚጠየፋቸው እኩይ ባህርያት ሲሆኑ በሚቀጥለው ርዕስ ሥር በቀረቡት ግጥሞች ተከውነዋል።

***1. ስርቆት***

ስርቆት (ሌብነት) ተጠኝው ማኅበረሰብ በመጥፎ ምግባርነት ከፈረጃቸውና ከሚፀየፉቸው ተግባራት ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው። እነዚህ ተግባራት ደግሞ በተለይ ለጀግናው እጅግ ፀያፍ መሆናቸውን ቀጥለው የቀረቡ መረጃዎች ያሳያሉ፡-

ከምቀኛው ጋር አታገኘኝም አለ አስናቀው
ከሌባው ጋር ግን አታገኘኝም፤ከነገር ስሪው አታገኘኝም
ከምቀኛው ጋር አታገኘኝም፣ አምላኬ ከላይ አልተጣላኝም።

እነዚህ ስንኞች ከዋኙ በሁሉን አወቅ ሶስተኛ መደብ የትረካ አንፃር አቅርቧቸዋል። በስንኞቹ ውስጥ ተናጋሪ ሆኖ የቀረበው ሟቹ ነው። ሟቹ ምቀኛን፣ ሌባን፣ ነገር አሾክሿኪን፣ ሲፀየፍ ይታያል። እሱ ጥፉፍ ባህርያት ካላቸው ሰዎች ጋር እንደማይውል ይገልፃል። ይህንን ማድረግ ከአምላክ ጋር መጣላት እንደሆነ ያለውን እምነት ይጠቅሳል። መሐላና ክህደትም ማህበረሰቡ ከጀግና የማይጠብቀው ባህርይ ነው።

***2. መሐላና ክህደት***

*ኸረ ግድያን አትታከኩ፤ኸረ መሃላን አትታከኩ፤ኸረ ክደሽን አትታከኩ*
*ከባድማችሁ ልጅ እንድትተኩ*
*እኔ አባታችሁ ብገደል ኑሮማ፤እኔ አጎታችሁ ብምል ኑሮማ*
*የት ይገኝ ነበር ይኸ ባድማ?*

ይህ መረጃ በተጠኝው ማኅበረሰብ ውስጥ ጥሩ ባልሆነ ዋጋቸው የሚታወቁትን ግድያ፣ ክህደትንና መሀላ የተሰኙ ድርጊቶችን ከዋኜ ያወግዛል። ተጠኝው ማኅበረሰብ ሌባንና ከሀዲን ይጠላል። እንደዚሁ ሁሉ መሀላ ውጤቱ ከባድ ነው ብሎ ስለሚያምን በአድርጊያለሁ፣ አላደረግሁም፤ ወይም በየእኔ ነው የአንተ አይደለምና በመሳሰሉ ምክንያቶች የተጣሉ ሰዎች በተቻለ መጠን መሀላን እንዳይምሉ፣ ይልቁንስ በመተማመን እርቅ እንዲያወርዱ ይመክራል። ብዙ ጊዜ ሰዎች ይህንን ምክር የሚሰሙ ሲሆን አልፎ አልፎ ግን መሐላውን መፈጸም የግድ ይሆናል። ማኅበረሰቡ በሀሰት የማለ፣ ወይም ጥፋት ያላጠፋን ሰው ያስማለ ሰው ጊዜውን ጠብቆ አንዳች መከራ ይወርድበታል ስለሚል በተቻለ መጠን መሀላ እንዳይፈፀም ይታገላል። ጀግኖችም መሀላን ይጠላሉ፤ ከሰው ጋር ክርክር በመጣባቸው ጊዜ፤ ጉዳዩን ለአምላክና ለማኅበረሰብ ፍርድ ሰጥተው ኑሯቸውን ይገፋሉ። እነሱ በዚህ ባለመማላቸው ወይም ባለማስማላቸው መከራ ይመጣብናል ብለው አይፈሩም። ይልቁንስ የተባረኩ ልጆች፣ ለልጅ ልጅ የሚተላለፍ ሀብት (ባድማ) ይኖራቸዋል።

## 7. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በባህር ዳር ከተማ፣ በሰባታሚት ቀበሌ ለቅሶን አጋጣሚ አድርገው በሚከወኑ ቃል ግጥሞች ውስጥ የሚገለጠውን የጀግና ብያኔ መመርመር ነበር። በትንታኔውም የፉከራ ቃል ግጥሙ ጋር በተያያዘ እያንዳንዱ ፉከራ የራሱ የሆነ የክዋኔ ቅርፅ አለው። ይህ ቅርፅ ክዋኔው የመግቢያ፣ የክወናና የመዝጊያ ቀመር አለው፤ በፉከራው ውስጥ የከዋኙን ሚና የሚጫወቱ ሁለት የትረካ አንፃሮች አሉ። አንደኛው በአንደኛ መደብ የሚነገረው የሟች ድምፅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በሦስተኛ መደብ የሚቀርበው የከዋኙና ታዳሚ የትረካ አንፃር ነው። እነዚህ የክዋኔ መልኮች

ፉከራው የሚከወንበትን ፋይዳ የሚያጎሉ ናቸው የሚሉ ውጤቶች ተገኝተዋል። በተተነተነው የፉከራ ግጥም ውስጥ ጀግና የሚባለው ማኅበረሰቡ ያበጀውን እሴትና ደንብ ማክበርና መጠበቅ የቻለ፣ በአንፃሩ ማኅበረሰቡ የተጠየፋቸውን ባህርያት የተጠየፈና ለማስወገድ የሚሠራ ሰው መሆኑን፤ ጠንክሮ በመሥራት የተገኘ ሃብት፣ የቤተሰብ ፍቅር፣ ትዳር፣ ኩነኔን ማሰብ (መንፈሳዊነት)፣የተጣላን ማስታረቅ (ሽምግልና)፣ ሁለገብ ዕውቀት፣ ጠንካራ ሠራተኛነት፣ እንግዳ መቀበል፣ ማኅበረሰቡ የሚጠየፋቸው ነገሮች፣ ስርቆት፣ ስንፍና፣ መሃላ፣ ክህደት የሚሉ ድርጊቶች ውስጥ አለመገኘት ሃሳቦች የጀግና መገለጫ መልኮች ሆነው ቀርበዋል፤ ለቅሶን መሠረት አድርገው የሚከወኑ ፉከራዎች መሠረታዊ ትኩረታቸው ሟችን ማወደስ፣ በሕይወት እያለ የነበረውን ስብዕና መግለፅ ቢሆንም አልፎ አልፎ የሟችን ማንነት ከመግለፅ አንፃር ሥራዬ ተብሎ የሚደረግ ግነት አለባቸው፣ በሥነቃሉ የቀረበው የሟች አካላዊና መንፈሳዊ ማንነት ሙሉ በሙሉ የግለሰቡ ትክክለኛ መልክ አይደለም። ይልቁንስ ማኅበረሰቡ ባበጀው ባህል ውስጥ መገለጫ የሆኑት እሴቶችና ደንቦች ትርጓሜ ነው። ጀግና የማኅበረሰቡን እሴትና ደንብ ማክበርና መጠበቅ የቻለ፣ ማኅበረሰቡ የተጠየፋቸውን ባህርያት የተጠየፈና እነሱን ለማስወገድ የሚሠራ ሰው ነው የሚሉ ውጤቶች ተገኝተዋል።

ከውጤቶች በመነሳት በከዋኝና በታዳሚ መካከል የሚደረግ የክዋኔ ተግባቦት የግለሰቡን ማንነት ብቻ፣ ሳይሆን በማኅበረሰቡ ዘንድ የሚጠበቅን ባህላዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያና ፖለቲካዊ ሰብዕና ለመትከል የሚደረግ ጥረት ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ተደርሷል። ርዕሰ ጉዳዩ በርካታ ሃሳቦችን አምቆ የያዘ በመሆኑ የባህል ጥናት ዕቅድ ያላቸው አካላት ጥናት ቢያካሂዱበት ሰፊና አዳዲስ ዕውቀቶችን ያበረክታሉ።

# ዋቢዎች


ማኅተመ ስላሴ ወልደ መስቀል። (1957ዓ.ም)*። አማርኛ ቅኔ ነጠላ፤* አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት

ሞገስ ሚካኤል። (2002 ዓ.ም.)። *የላይ አርማጭሆ ማህበረሰብ የጀግና የቀብር ስነስርዓት፣* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ።

ባይለየኝ ጣሰው። (1993 ዓ. ም)። *ኦቴና፣ የአኙዋ ባሕላዊ ጀግና፣* አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ፕረስ።

ብርሀኑ ገበየሁ። (1995 ዓ. ም) ። *የስነቃል ምንነት፣ ዘውጎችና አተናተን።* አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል። ያልታተመ።

ጌትነት ይርሳው። (2011ዓ.ም) ። የጀግና እሳቤ በይጎማ ሁለቱ ማህበረሰብ የጀግና የለቅሶ አውድ ውስጥ በሚከወኑ የፉከራ ቃል ግጥሞች ይዘትና ክዋኔ ውስጥ፣ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ በፎክሎር ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ።

ዘሪሁን አስፋው። (1992 ዓ. ም)። *የስነጽሑፍ መሠረታውያን።* አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ቤት።

የባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ግብርና ልማት ፅ/ቤት። (1999 ዓ.ም.) ። *የወረዳው እምቅ ሀብቶች*። ባህር ዳር፣ ማተሚያ ቤት የለውም።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፣ *አማርኛ መዝገበ ቃላት።* (1993 ዓ.ም) ። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ፈቃደ አዘዘ። (1991) ። *የስነ -ቃል መምሪያ፤* አዲስ አበባ፤ ኢትዮ ጥቁር አባይ አሳታሚዎች።

ፈቃደ አዘዘ (አዘጋጅ)። (1975 ዓ.ም.)። *‹‹ስለ ስነጽሑፍ 13 መጣጥፎች መድበል››።* ያልታተመ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል።

Abrams, M.H. (1981). *A Glossary of Literary Terms*. 4th ed. Canada. Holt.

Bascom, W. R. (1954). Four Functions of Folklore. *The Journal of American Folklore*, *67* (266), 333-349, American Folklore Society.

Barkan, S. E. (2011), Sociology, Understanding and Changing the Social World. *Faculty and Staff Monograph Publications*. https:// digital commons. Library umaine. Edu/fac_ monographs/2

Bauman, R. (1975). Verbal art as performance. *American Anthropologist*. New Series *77*. (2). 290 – 311.

Ben-Amos, D. (1971). Toward a Definition of Folklore in Context. *84*, (331), *the Journal of American Folklore Society.*

Bronner, SJ. (1988). “Art, performance and praxis: The Rhetoric of Contemporary Folklore Studies”, *Western folklore*.vol *47*, (2), 75 -10.

Campbell, J. (1990). *The Hero with a Thousand Faces* Bollingen Series, (17).

Carlyle, T. (1998) *On Heroes, Hero Worship and the Heroic in History* [J]. University of Adelaide Library.

Dundes, A. (1986). The Anthropologist and the Comparative Method in Folklore *Journal of Folklore Research*. USA, Indiana University Press *23* (2/3), Special Double Issue:

Finnegan, R. (1970). *Oral Literature in Africa*. Cambridge, UK: Open Book Publishers, http:// · dx.doi.org/10.11647/OBP.0025.

Finnegan, R. (1977). *Oral Poetry: it's Nature, Significance and Social context.* Bloomington and Indiana Sound and Sentiment, Indiana University Press.

Finnegan, R. (1992). *Oral Traditions and the verbal Art*. Routledage, Inc. NewYork, Macmillan Ltd, New York.

Hymes, D. (1975). "Breakthrough in to performance": *In APPROACHES TO SEMIOTICS*. Netherlands, Library of Congress.

Kapchan, D. A (1995). Performance. *The Journal of American Folklore*. University of Llinois press, *108* (430), 479- 508.Autumn

Luigi, K. (2003). *Hero as the Cultural Ideal.* Harvard University Press: Cambridge, Massachusetts.

Labarge S. (2010). *Why Heroes Are Important*. Santa Clara University.

Miriam B. (2017). *What Is the Function of a Hero in Our Society?* California.

Orrin E. Kl. (1948). *The Creation of Popular Heroes*. American Journal of Sociology, *54,* the University of Chicago Press.

Peter, J. (2010). *Anthropoplying Cultural Anthropology* 5th Education. University of Northern Iowa and Emory

Roebuck K, RJ. (2008). *Extraordinary Acts by Ordinary People* [J]. China today: English version.

Sims, Martha.C. And Stephens, Martine. (2005). *Living Folklore: An Introduction to the Study of People and their traditions*. Utah state university press, USA.

Stewart W. (2006). *Collins's dictionary of law*. 2nd ed. free reins entertainment, Amazon. *International Encyclopedia of the Social Sciences*.

Thompson, J.A. (2005). Proactive Personality and Job Performance: Asocial Capital Perspective.

**የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር መግለጫ**[12]

| ተ.ቁ. | ሙሉ ስም | ፆታ | እድሜ | የመኖሪያ አድራሻ | ስራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ደባሱ ፈንታሁን | ወ | 58 | አባራጅ | አርሶ አደር |
| 2 | አቶ በለጠ አስናቀው | ወ | 51 | ሰባታሚት | አርሶ አደርና ነጋዴ |
| 3 | አቶ በላይነህ ፈንታሁን | ወ | 38 | ባህር ዳር | አርሶ አደር |
| 4 | አቶ ፀጋ አስናቀው | ወ | 64 | ሰባታሚት | አርሶ አደር |
| 5 | አቶ ተመስገን ፈቀደ | ወ | 56 | ሰባታሚት | አርሶ አደር |
| 6 | አቶ ይመኑ እውነቴ | ወ | 40 | ሰባታሚት | አርሶ አደርና ነጋዴ |
| 7 | ወ/ሮ አለም መኮንን | ሴ | 70 | አባራጅ | አርሶ አደር |
| 8 | ወ/ሮ አስማሩ ፈንታሁን | ሴ | 57 | አባራጅ | አርሶ አደር |
| 9 | አቶ መሰንበት አስማረ | ወ | 36 | አባራጅ | ገበሬና ነጋዴ |

[12] መረጃ ሰጪዎቼ ላደጋችሁልኝ ሁለንተናዊ ድጋፍ አመሰግናለሁ፡፡